## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## <u>አራተኛ የኢትዮጵያ ሁለተኛ የኬንያ ጉዞ</u>

እግዚአብሔር አምላክ ሆይ «እስመ ዘእንበልየሰ አልቦ ዘትክሉ ገቢረ ወኢምንተኒ» የአለ እኔ ምንም ምን የምታደርጉት የለም» ብለሐልና ይህንን ሰኞ ጥር 25 ቀን 2001 የማደርገውን የሁለት ሀገራት ጉዞ እንድት ባከርክልኝ በጉዞየ ሁሉ እንዳትለየኝ እለምንሃለሁ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

ይህ የሚያካትተው በጉዞዬ የአየኋቸውን የሰማኹቸውን የተፈጸሙ ድርጊቶች የአጋጠሙ ችግሮች የሚመዘግብ ይሆናል፡፡

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ሰኞ ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም አዲስ አበባ ደርሻለሁ፡፡የነበረ መልካም ነገር ዳላስ አውሮፕላን ማረፍያ ቀደም ብዬ ስደርስ ለችግረኞች የተያዘው በዛ ብለው እንዲቀነስ ስንጠብቅ ቆይተን የአገኘነውን ተራ ለሌላ ተሰጠ ከዚያ የኤርፖርቱ ሠራተኛ ወ/ሮ ራኄል ተፈልጋ ያለምንም ጥያቄ እንዲላክ በመደረጉ የአለምንም ችግር ዕቃው ሁሉ አለፈ በዳላስ ኤርፖርት ሁሉም መልካም ነበር፡፡

አውሮፕላኑ በ8 ሰዓት የተባለው በ10ሰዓት ተነሳ በአውሮፕላኑ ውስጥ አቶ እንዳለን አገኘሁት የአለፈውን የወደፊቱን ስነጋገር ሳይታወቅ ሮም ደረስን ሮም ለአንድ ሰዓት ይቆይ የነበረው ከሁለት ሰዓት በላይ ቆጠይቶ በጥሩ መስተንግዶ ቦሌ ደረስን ለችግረኞች የተያዘው ዕቃ በመጥፋቱ እሱን ስንፈልግና በመጠበቅ ከሁለት ሰዓት በላይ ሰዓት አጠፋን ያም ሆኖ ዕቃው ሳይገኝ ሐሙስ ይመጣ ይሆናል ምንም ማደረግ አይቻልም ብለውን ወጣን ይህ ትንሽ የአጋጠመን ችግር ነበር፡፡

ወ/ሮ ጽጌ /ወ/ሮ ረኄል መኩርያና ሌሎችም ተቀበሉን ወደ እነአቶ አደላ ቤት ሄድን ምሳ በልተን ከመምህር ዘለዓለም ጋር ቀጠሮ ስለአልን እሱን እየጠበቅሁ ነው ፡፡ወዲያው ዲያቆን ዘለዓለም መጣ ቀኑ ዮሴፍ ስለነበር ጉባዔ ስለነበር ተያይዘን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ፡፡ ሕዝቡ አውደ ቤተ ክርስቲያኑን ግጥም ብሎ ሞልቷል ፡፡ ከእሱጋር ሁለት ወጣት ሰባክያን

የተለመደ የምዕመናንን ልቡና በሚያረሰርስ ሁኔታ ትምህርት ሰጡ በምርጥነሽና በልዑል ሰገድ መሪነት በሰንበት ት/ቤቱ አጃቢነት በሕዝቡ ተባባሪነት የተለያዩ መዝሙራት ቀረቡ።
የሕዝቡ ለቃለ እግዚአብሔር የአለውን ፍቅርና ፍላጎት ሲታይ ምግቡም መጠጡም ይህ እንደሆነ ይገመታል ጠጠር ለመጣያ ቦታ አልነበርም በዚህም እግዚአብሔርን አመሰገንኩ በጣምም ደስ አለኝ።ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ላይ አልቆ ወደ ማረፍያ ቤቴ ሄድኩ።

## በማግስቱ ረቡዕ ጥር 27 ቀን የጅማ ጉዞ

ጧት ዘጠኝ ሰዓት አቶ ጌራ ሚካኤል ብርሃኑ ቀሰቀሰኝ ጉዞ በአቡነ ሐራ ስም የተቋቋመው ማኅበር አባላት በአንድ ትልቅ አውቶቢስ እኔና መጋቤ አእላፍ አባ ተክለ ሃይማኖት ከብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ጋር በመሆን የጋራ ጸሎት ከተደረገ በኋላ በብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ መኪና መሪነት በ1999 ዓ.ም ክርስቲያኖች በአክራሪ ሙስሊሞች ወደ ተረሸኑበት የሚያደርሰውን መንገድ በመጀመር ወሊሶን ወልቅጤን አልፈን የግቤ ወንዝ አቋርጠን  አበልቲ ኪዳን ምሕረት ገዳም ለመድረስ አቀበቱን ተየያዝነው እግዚአብሔር ይመስገን እኩለ ቀን ሳይሆን ገዳሙ ደረስን።

ገዳሙ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዘመን የተመሠረተ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ግብር ለዚች ቤተ ክርስቲያን እንዲያስገባ እንደ ደነገጉና ገዳሙ በዚህ እንዲተዳደር አድረገው እስከ ደረግ ጊዜ እንደቆየ አገልግሎቱ በደርግ ጊዜ  ለተወሰነ ጊዜ በመቋረጡና ቤተ ክርስተያኑም አዝሞ እንደፈረሰ በ1982 ዓ.ም. ተመልሶ ይህ አሁን የምናየው ቤተ ክርስቲያን እንደተሠራ ገለጻ ተደርጎልናል ከተለያዩ ብሔረሰብ የተለያዩ ቋንቋ ከሚናገሩ ተመርጠው በአዳሪነት የሚማሩ ከአርባ በላይ የሆኑ ህፃናት እነሱን የሚያስተምሩ መምህራን በሞግዚትነት የሚያገለግሉ መነኮሳይያት እንዳሉ ተመልክተናል ኑሮአቸው በተአምር እንደሆነ ገለጻ ተደርጎልናል። ማኅበረ ቅዱሳን ለአዳሪ ተማሪዎች 36 ክፍል ከእነሙሉ አገልገሎቱ አሠርቶ ለማስረከብ በማለቅ ላይ የአለውን መኖርያ ቤት ተመልከተናል። አካባቢው በከፍታ ቦታ ላይ ስለተመሠረተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ያሳሰባል በረሐማ በመሆኑ ገዳመ አስቄጥስን ይመስላል በጣም የሚያስደስተው የግቤ ወንዝ መቀነትነት ነው ቦታውን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊጎበኘውና ሊደገፈው የሚገባ ነው።

ብፁዕነታቸው ስለገዳሙ አሠራርና ሕይወት ሠፊ ገለጻ ድርገዋል፡፡ የአለባቸው ችግር ለጊዜው ሦስት እንደሆኑም ጠቁመዋል፡፡ እነርሱም

1. አካባቢው ከመስከረም ወር ጀምሮ ኅዳር አስከሚታጠን የወባ ትንኝ እንዳለባቸው ህጻናቱ ሲታመሙ ክሊኒክ በአለመኖሩ አንዱ ጧት ታሞ ወልቅጤ ሲወሰድ ሌላው ደግሞ አድርሰው ሲመለሱ ታሞ እንደሚጠብቃቸው እንዲሁም የክሊኒኩ መኖር ለገዳሙ ብቻ ሳይሆን ለአካባቢውም ኅብረተሰብ ጭምር ማገልገል እንደሚችል አስገንዝበው ይህንን በተመለከተ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለተለያዩ ደርጅቶች የላክን ሲሆን አንደኛው ገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፈስ አድን ኮሚቴ ነበር ይህ ኮሚቴ ቀደም ሲል ክርስቲያኖች በታረዱበት ወቅት ከሁሉም በፊት የደረሰላቸው መሆኑን በአድናቆትና በምስጋና አስታውሰዋል፡፡ ይህንንም በተመለከተ በትልቅ  የመንግሥት ስብሰባ ላይ የመጀመርያው ለችግሩ ደራሽ  በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ስም  ይህ ድርጅት እንደሆነ ተደርጎ ሪፖርት ቀርቦ እንደነበር የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስካጅ ሊቀ መዘምራን ገልጸውልናል፡፡

2. ህፃናቱ በሁሉም ሙሉ ሆነው እንዲያድጉ ዘመናዊ ትምህርት ያስፈልግ ነበረ፡፡ ያ የለም ከዚህ በፊት ትምህርት ቤቱን ለማሰራት ኃላፊነት ወስደው ዕቃ ሁሉ አስመጥተው ሥራውም እንደተጀመረና እንደቆመ ጅምሩንና ዕቃዎቹን ተመልክተናል፡፡

3. ውሃ ማስወጣትና ከገዳሙ ኩታ ገጠም ቦታዎችን መግዛትና ገዳምያኑ እራሳቸው እየሠሩ እንደሌሎች ገዳማት ለሌላውም የሚተርፉ እንዲሆኑ ለማድረግ ቦታ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ከዚያም ህፃናቱ በተለያዩ ቋንቋዎች መዝሙር ከአሰሙን በኋላ በዚያ የሚደረገው የሥራ ጉብኝት ተፈጸሞ በጸሎት ከተደመደመ በኋላ ወደ ሌላው አመራን፡፡ አበልቲ ኪዳን ምሕረት ገዳም የአለበት ቦታ ከአዲስ አበባ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሲገኝ የጅማ መንገድ ላይ ነው የአለው፡፡

ከዚያ ዝቅ ብሎ እራስ መስፍን አሠርተውት ወደ ነበር የቁቢ-ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አመራን በዚያ አካባቢ የአሉ ከአሥራ ስምንት ቤተ ሰብ የማይበልጡ በሺህ በሚቆጠሩ የእስልምና ተከታዮች ተጽኖ እየተደረገባቸው የአሉ በበርካታ መስጊዶች የታጠሩ ይገለገሉበት የነበር ቤተ ክርስቲያን ከፈረሰ ተለይቶ የማይታይ አናሳነታቸው እንዳይሰማቸው በማስብ የአቡነ ሐራ ማኅበርተኞች በአቶ ጌራ ሚካኤል ብርሃኑ

አሰተባባሪነት የተጀመረውን አዲስ ቤተክርስቲያን ተመልክተናል፡፡ ስለአሠራሩም ገለጻ ተደርርጓል የገንዘብ ማሰባሰብ መርሐ ግብር ተካሂዷል ከዚያ አነስተኛ ሰው 24 ሺህ የኢትዮጵያ ብር ተሰበሰቧል፡፡

በመቀጠል በጣም አክራሪ ሙስሊሞች ወደሰለጠነቡት ናዳ ኪዳን ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አመራን ከመንገድ ወጣ ብሎ የኮረኮንች መንገድ ስለነበር ከፍ ዝቅ ማለቱ ነበር ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ወጣቱ እየዘመረ ሕዝቡ እልል እያለ ተቀበለን በገጻቸው ላይ የሚነበበው በአክራሪው ምን ያህል ሰቆቃው እንደበዛቸው ያሳይ ነበር በዚህ ወረዳ አምስት አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ ሦስቱ በአክራሪው ወረራ የተነሳ ካህናቱ ለቀው ስለሄዱ ከተዘጉ እንደሰነበቱና በወር ለአንድ ካህን 200 ብር ከተገኘ መልሶ መክፈት እንደሚቻል ሪፖርት ቀረበ በዚሁ መሠረት ለርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቤተ ክርስቲያን እናቀርባለን ብትፈቅድ እንደትሸፍን ያም ባይሆን እኔና ራኄል መኩርያ መሸፈን እንደምንገደድ በመወሰን ለሦስት ካህናት በየወሩ ስድስት መቶ የኢትዮጵያ ብር ተከፍሎ አብያተ ክርስቲያናቱ በአስቸኳይ እንዲከፈቱ አድርገናል፡፡ በዚያ የነበረው የምእመናኑ የፍቅር አቀባበል ሲቃ ያሲዛል ከዚያው ከአለቻቸው ተለቅተው የአቀረቡት መስተእንግዶ በጣም የሚማርክ ነበር አባታችን ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ማጽናኛና መመርያ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው ወደ ደነባ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጉዞ ሆነ፡፡

አቀባበሉ ከናደ ኪዳን ምሕረት የተለየ አልነበረም የግቤ የኤሌትሪክ ማማንጫ ሠራተኞች በአካቢው የሠፈሩ ስለሆነ የተሻለ ሁኔታ ይታይበታል በቤተክርስቲያኑ አጠገብ ካለ ትልቅ የመሰበሰቢያ አዳራሽ ገባን ሪፖርት ቀረበ በአለፈው ዓመት ይህ አዳራሽ እንደተጀመረ እህታችን ወ/ሮ ራኄል መኩርያ ከአሥራ ሁለት ሺህ ብር በላይ ለአዳራሹ እንዳወጣችና በስሟም እንዲሰየም ለሊቀ ጳጳሱ አቅርበው ለማስፈጸሚያ ከአሥራ አምስት ሺ ብር በላይ እንደሚያስፈለግ ተጠየቀ፡፡ ሊቀ ጳጳሱም ስያሜውን አጽድቀው «ማኀደረ ራኄል» ብለውታል፡፡ እሷም አሠራራቸውን ትጋታቸውን በማድነቅ ቀሪውን በማውጣት ለማስፈጽም ቃል ገብታለች፡፡

ከዚያም ጅማ ከተማ መዳረሻ ወደሆነው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ገባን ሪፖርት አዳመጥን እርዳታ ለአጥር ማስፈጸሚ ተጠየቀ እርዳታ ተሰበሰበ ወደ መንበረ ጵጵስና አመራን፡፡ በዘያ ቦታ ምሽት ሰለደረስንና

ድካምም ስለነበር የአለውን ሁኔታ በመልስ ጉዞ ይመዘገባል፡፡በመነበረ ጽጽስናው እራት በላን አዳር በዚያው ሆነ፡፡

## *ሦስተኛው ዕለት ሐሙስ ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም*

ጧት ለክ በአስራ አንድ ሰዓት በመነሳት በብፁዕ አቡነ አስጢፋኖስ መሪነት «የሃያ አንድኛው ክፍለ ዘመን ሰማዕታተ ኢትዮጵያ» ወደ ተረሸኑበት በሸሻ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ስናመራ እግር መንገዳችንን የእስላሞች መነሐርያ የነበር ክርስቲያኖች በፍርሐት ብቻ መኖራቸው የማይታወቅ በጣም በጣት የሚቆጠሩ ቢኖሩም የሚገለገሉበት ቤተ ክርስቲያን አልነበራቸውም በዚህ ምክንያት የአንድ ክርስቲያን ልጅ ሙቶ የሚቀብርበት በማጣቱ አባቱም ሚቹም ሳይቀር ሰልሞ በእስልምና ሥርዓት መቀበሩን የሰሙ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ምዕመናን በማስተባበር የአቡነ ሐብተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሰርተውላቸው ወደ ነበረው ጎራ በማለት ኪዳን አድርሰን ሰማዕታተ ኢትዮጵያ የተቀበሩበትን ደርሰን ስለአፈጻጸሙ አረመኔያዊ ድርጊት ብፁነታቸው ሲገልጹ ሰድስት እንደነበሩ ከእነሱም መካከል

1.ቀሲስ ከፍያለው ይግለጡ
2.ቀሲስ ጌትነት ወልዱ
3.ወ/ሮ ዓለምነሽ ደበላ
4.ወ/ሮ ምሕረት ረዳ
5.አቶ ተፈራ ተከተሌ
6. አቶ አቦየ በየነ

እንደነበሩና ሁሉም ከተለያዩ ብሔረ ሰብ እንደ ነበሩ በተለይ ሁለቱ ሴቶች «አላህ ክበር» ብላችሁ ክራችሁን በጥሱ እንተዋችኋለን በማለት በማስፈራራት ከግማሽ ሰዓት በላይ እንደለመኗቸውና እነሱም አንገታችን ይበጠሳል እንጂ ክራችን አየበጠሰም በማለት በእምነታቸው ስለፀኑ በዲቢዲው እንዳያችሁት በአሰቃቂ ሁኔታ ሰማዕትነትን ተቀብለዋል ወ/ሮ ዓለምነሽ ንስሐ ገብተው ሥጋውን ደሙን ለመቀበል ነጭ ልብሻቸን ለብሰው እንደመጡ የክብር የሰማዕትነትን ዋጋ እንደተቀዳጁ ጨምረው አሰምረውበታል፡፡

በመቀጠልም ቤተ ክርስቲያናችን ትኩረት ሰጥታው ቢሆን እሰከአሁን ቤተ ክርሰቲያኑ ተሠርቶ መታሰቢያቸው ቁሞ በአየነው ነበር ይህ የምታዩት

መቃኞና ደረጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ለጊዜው የአሰሩት በጎ አድራጊዎች ናቸው::አሁንም በጎ አድራጊዎች ቤተ ክርስቲያኑ እንዲሠራ መታሰቢያቸው እንዲቆም ገዳም እንዲገደም በማለት ኃሣብ የሚያቀርቡ እንዲሁም በአለፈው እናንተ ከምትኑሩበት አትላንታ ጆርጅያ ከሚባል ሥፍራ ስድሳ ሺ ብር ተልኮልናል::ቅዱስ ሲኖዶስም ከአቅም እጦት የተነሳ ነው እንጂ የኃሣቡ ደጋፊ ስለሆነ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ አስከ አሁን እንደ አደረጋችሁትና እንደምታደርጉት በውስጥም በውጪም የአላችሁ ማኅበረ ምዕመናን እንደትተባበሩና እንድታስተባብሩ አደራ በማለት ጸሎተ ቡራኬ ስጥተው አጋሮ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሄድን በዚያም ሪፖረት ሰምተናል የቁረስ መስተእነግዶ አደርገውልናል በሪፖርታቸውም ቤተ ክርስቲያኑ ለዚህ አካባቢ የመጀመርያው አንጋፋ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነና በዘመን ብዛትና በጥገና አሠራር ጉድለት እያፈሰሰ መሆኑን አሳስበው እርዳታ ጠይቀዋል እዚያው ከአለነው ተሰበሰበ ቃልም ተገባ እኔንም ቃል እንድገባ ለእርዳታው ተጠይቄ ወደ መጠሁበት ተመልሼ ቤተ ክርስቲያኔንና ማኅበረ ምዕመናኑ በመጠየቅ የሚቻል ነገር ከአለ ለማስተባበር እሞክራሉ በማለት ኃሣብ ሰጥቼ በዚህ የአለው መርሐ ግብር ተፈጽሞ ጉዞ ወደ መቱ::

በዚሁ ዕለት የመቱ ጉዞ ወደ ኤሉባቡር ጉዞ በጉዞው ብፁነታቸው ቀደም ብለው የያዙት መረሐ ግብር ስለነበር በዚህ ጉዙ ላይ አለነበሩም ብፁዕነታቻው ባይኖሩም ሹፌራቸውንና የአስተዳደር መመርያ ኃለፊ የሆኑትን አቶ ሰሎሞን እንዲሁም መኪናቸውን ከእነ ነዳጁ በመፍቀድ ትልቅ ትብብር አደርገውልኛል ለቤተ ክርስቲያን የአላቸው ሐዋርያዊ እንቅስቃሴ በቃላት መግለጽ ባይቻልም በዚህ አጋጣሚ ስለአደደረጉልኝ ትብብር በራሴና በርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅደስተ ማርያም ስም ታላቅ ምሰጋናየን በማቀረብ ጉዞው ሲዘገብ ጉዞ አስደሳችና አድካሚ ነበር መቱ በአሥራ አንድ ሰዓት ስንደርስ ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስንደርሰ ካህናት ወጣት መዘምራንና ምእመናን ተቀብለውናል::

ይቀበሉናል ብለን እንጠብቅ የነበረው የመቱ ሥራ አስካጅ ሊቀ ትገሃን ብርሃኑ መንገሻ አልነበሩም:: እቢሮአቸው ሆነው እኛ ወደ እሳቸው እንድንመጣ መልክት አስተላልፈዋል:: በመሠረቱ ሊቀ ተጉሃን በ1999 ዓ.ም በአክራሪው ለተጎዱት ወገኖቻችን በገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን የመጀመርያው ደራሽ በመሆን እርዳታ የሰጠው በእሳቸው አማካይነት ስለነበርና ሠርተው እራሳቸውን የሚረዱበት ለእንጨት ሥራ አግልግሎት የሚሆን ቤት እንዲሠራላቸው መሣርያው እንዲገባለቸው

ፕሮፖዛል አቅርበው ይህንኑ በሰሜን አሜሪካ የከህናትን የምዕመናን ጉባዔ የተቸረ ሲሆን እንዲሁም መምህራን ለአልተመደበላቸው አምስት ወረዳዎችም ገንዘብ መድቧል ይህ ገንዘብ የተፈቀደላቸው ማለትም መልሶ የሚያቋቁሙ መምህራን የሚያስማሩበት ገንዘብ ከድርጅቱ የተላከ ስለነበር ይህ ገንዘብ ምንያህል በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን አረጋግጬ እንድመለስ ኮሚቴው ስለጠየቀኝም ከእሳቸው ጋር እንደገናኝ አስፈላጊ ስለነበር ወደ አሉበት ሥፍራ ቢሮአቸው ተጓዝን እንደ ደረስንም በእሳቸው ላይ የሚታው የመደንገጥ መንፈስ ነበር ለሰባክያነ ወንጌል የተላከው አምስት ሺ ዶላር እንዴት? ለማን? አከፋፈሉስ በምን መልኩ ነበር? ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ በመሠረቱ ለአምስት መምህራን እንዲመደብ መመርያ ተሰጥቶኝ ስለነበር ተፈርሞ የአለለቀ የአራት ሰባክያን ዝርዝር የአለበት ሂሣብ ሹሙ ብቻ የፈረመበት ለማስየት ሞከሩ አቶ ጌራሚካኤል ብርሃኑ ይህማ በሂሣብ አሠራር ልክ አይደለም ሲሉ ጣልቃ ገቡ በቂ መልስ አላገኙም ሁለተኛው ጥያቄ መምህራኑን ይጠሩልናል ልናነጋግራቸው እንችላለን? አይቻልም እነሱ የአሉት በየወረዳው ነው ለዚያውም በየጊዜው ስለሚለዋወጡ ቋሚ አይደሉም ሲለቁ ወዲያው እየተከን ነው ቋሚ መምህራን የሉንም የተሰጠንም ገንዘብ ጊዜያዊ በመሆኑ ነው ሲሉ መልሰው በዚያን ዕለት የሠሩት ቅጽ እንደሚያሳው ከማኅበሩ ከተሰጠው ከወጪ ቀሪ ሃያ አራት ሺ ብር መሆኑንን የሚያሳይ ለማቅረብ ሞክረዋል፡፡ እንዲሁም የተሠራውን እንጨት መሰንጠቂያ ሥፍራ ወሰዱን የቤቱ ሥራ ከዚያ ቀደም ወ/ሮ ራኄል መኩርያ ሪፖርት በዚያ አቾጋሪ መንገድ ሁለት ጊዜ በመመላለስ ከአቀረቡልን ሪፖርት የተለየ ነገር እንደሌለው ወ/ሮ ረኄል መኩርያ በቦታው ስለነበሩ ገልጸዋል፡፡ በመሠረቱ ስለቤቱ አሠራር ባለሙያና ልምድ የአለው ኃሣብ ሰጥቶናል የሀገሩን ገበያ በትክክል ባናውቀውም በነገሩን መሠረት በዚያን ጊዜ በነበረው ገበያ ትክክል እንደሆነ ሊመስለን ችሏል፡፡ ለምን ቢባል ማኅበሩ ለቤቱ ማሰርያ ተብሎ የሰጠው አራት ሺ ዶላር ነበርና በወቅቱ ምንዛሪ ሲታሰብ መቀራረቡን ያስረዳልና፡፡ስለመምህራኑ በሰጡን ማስረጃ መሠረት ከመቀበል በቀር ልናጣራ የአደረግነው ሙከራ ሁሉ ውጤታማ ሆኖ አላገኘነንም ከጊዜ አንፃርም የእኛም እዚያ መቆየት በቂ ስለአልነበር ነውና፡፡በአጠቃላይ የሊቀ ትጉኃን አሠራር መቶ በመቶ እምነት ባይጣልበትም አቶ ጌራ የኢትዮጵያው ተወካያችን ወ/ሮ ራኄል የኮሚቴው አባል ሰባ አምስት በመቶ በመቀበል የጠየቁት የእንጨት መሰንጠቂያው መሣርያ እንዲገዛላቸው ስምምነት ደርሰዋል፡፡ እኔም ቢሆን ከሀገሪቷ ተጨባጭ የአሠራር ሁኔታና ይህ ቤቱ የተሠራበት ቦታ በዚህ ዓይነት ሁኔታ

ከአልተያዘ መንግሥት ገንዘብ ላላቸው ሰዎች ስለሚሰጠው ቦታውን እንኪን በመጠበቅ ጀረጃ ስለሚጠቅም ከቦታው ሡፋትና መሐል ከተማ መሆን የተነሳ ገንዘቡ ሳይሆን መሳርያው ተገዝቶ ቢስጥ የማይከፋ መሆነን ሳቀርብ ታማኝ ሰው መታጣቱ እያሳዘነኝ ነው፡፡

## አራተኛ ቀን ዓርብ ጥር 29 ቀን ወደ ጋምቤላ ጉዞ

ዓርብ ከጧቱ በስድሰት ሰዓት ከመቱ ወደ ጋምቤላ ጉዞ በመንገድ ላይ እግር መንገዳችንን ፋሽሽት ኢጣሊያን አውግዘው ሰማዕትነት የተቀበሉ አቡነ ሚካኤል ሰማዕተነትን የተቀበሉበትን ቦታ እነ አለቃ አስረስ በእልቅና ሲመራዋት ነበሩትን ጎሬ ማርምን ተመልክተናል በአለቃው አማከይነት እቃቤቱን ጥንታዊውን ቅርስና የብራና መጻሕፍት ተመልክተናል፡፡ኤሉባቡር በአጠቃላይ ሡፊ ክፈለ ሀገር ነው ደኖች የሚያስደስቱ ናቸው ባሮ ወንዝ የጋቤላና የኤሉባቡርን የሚያዋስን ሲሆን በጣም በርካታ ውሃ ያለምንም አገልግሎት በከንቱ የሚፈስ መሆኑን ተረድቻለሁ ሙቀቱ እጅግ ኃይለኛ ነበር ሆኖም ባሮን አለፍ እንዳልን የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር መኪና በመላኩ ኤሲ(ማቀዝቀዣ) የአለው በመሆኑ ወደዚያ በመዛወር ነፍሴ ተነፈሰች፡፡ወደ ዋናው ከተማ መዳረሻ በሞተር ባይስከል ታጅበን ስንገባ ሆሣዕናን ያስታውሳል የከተማው ውበት የባሮ ወንዝ ድልድይ ርዝመት በጣም ያስደንቃል ኢሮፐንንም ከተሞች ለመምሰል ጥቂት ይቀረዋል፡፡ የሀገሩ መንበረ ጵጵስና ና ገዳሙ በአለበት እንደደረስን ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በደስታና በዝማሬ ተቀብለውናል፡፡ ከሰባ የሚበልጠው ሁሉ በነዋሪዎች ምዕመናን አማካይነት ሁሉ እግራቸው እንዲታጠቡ ተደረገ፡፡የፍቅር ምልክት ነበር የእንግዳ አቀባበላቸው በጣም የሚያስደስት ነው፡፡ቀኑ ዓርብ በመሆኑ የተዘጋጀው የጾም ምግብ በመሆኑ ምሳ ቀረበልን በላን ገዳሙን ሥፋቱ ከዚህ መለስ አይባልም በግምት ከሁለት ጋሻ ይበልጣል የግብፅ ገዳመ አሰቄጥስን ይመስላል የኢትዮጵያ ምእመናን ቢተባበሩ ከገዳመ አስቄጥስም የሚበልጥ ሊሆን ይችላል እግዚአብሔር የጎዝበ ክርስቲያኑን ልቡና ይክፈትላቸው፡፡ ከዘህ በኋላ ጃንሆይና አቡነ ባስልዮስ ወደ አሡሩት መሐል ከተማ ተጓዝን የማታ የትምህርት ፕሮ ግራም ተካሄደ ዝርዝር መርሐ ግብር በዲቢዲ ተቀርጻል፡፡ ያን ይመልከቱ፡፡

## አምስተኛው ቀን ቅዳሜ የካቲት 30 ቀን በጋምቤላ የተደረጉ

ጧት ተክሊል ስለነበር በተክሊሉ ላይ መገኘት ቅዳሴ ማስቀደስ ትምህርታዊ ምክር መስጠት ዝርዝር ሁኔታው በዲቪዲ ተመዝግቧል፡፡ ከሰዓት በኋላ የቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያንና የየቅዱስ ገብርኤል አብያተ ክርስቲያናት ጎብኝተናል በሁለቱም እርዳታ ተለግሷል ዝርዝሩን በዲቪ ተመዝግቧል፡፡

## ስድስተኛ ቀን እሁድ የካቲት 1 ቀን 2001 የከፋ ጉብኝት

ቅዳሜ ለእሁድ አጥቢያ የጋምቤላን የሥራ ጉብኝት በመፈጸም አዳር በዚያው በማድረግ ጧት በአሥራ አንድ ሰዓት ጉዞ ወደ ከፋ ከልል አመራን ጉዞው የመሬቱ አቅማመጥ ተፈጠሮ የአደለው አየሩ ተስማሚ ሙቀትም ቀዝቃዜም የሌለው ግራና ቀኝ ሲመለከቱት ምድራዊ ገነት ጉዞው ረዥም ቢሆንም ከውበቱ የተነሳ ድካም አይሰማም ነበር፡፡ ከምሶ ብሔረ ሰብ የአለበት በመናፍቃንና በእስልምና የተከበበ አቡነ ሀራ ገዳም ደረስን የአቡነ ሐራን ቤተ ክርስቲያን እራስ ተሰማ የተከሉት ሲሆን ገዳም እንዲገደም የአደረጉት በወቅቱ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ እስጠፋኖስ እንደሆኑ ተረድቻለሁ ፡፡ ቤተ ክርስቲያኑን በአዲስ መልክ የአሳነጹት በወቅቱ የካባቢው ሀገረ ስብከቱ ሰባኬ ወንነጌል የነበሩ አባ ተክለ ሃይማኖት ናቸው እሳቸውም ዛሬ የጋቤላ ሥራ አስንጅ ናቸው ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከምን መለስ ድረስ አልተለዩንም ከምሽቱ አሥራ አንድ ሰዓት ገዳሙ ደረስን የዋዜማ መጨረሻ ላይ ደረስን ጸሎት አድርሰን ወደ ማረፊያ ቤት ተጓዝን እራት ቀረበ በላን እረፍት አደረግን ከሌሊቱ ስድሰት ሰዓት ሥርዓተ ማኅሌቱ ተጀመረ ጧት በአራት ሰዓት ታቦተ ህጉ ወጣ ትምህርት ተሰጠ በዓመት ከየቦታው ከሚሰበሰብ ሙዳየ በረከት በሚገኘው ገቢ ስለሆነ የገንዘብ ማሰባሰብ መርሐ ግብር ነብር የገንዘቡንም ማሰባሰብ መርሐ ግብር የአካሄደው የጅማ ሀገረ ስብከት ሰባኬ ወንጌል ነው፡፡ ከትምህርቱ ጋር በማገናዘብ ጥሩ የገንዘብ ማሰባሰብ ችሎታ የአለው ወጣት ነው ለተወሰነ ጊዜ ለገንዘብ ማሰባሰብ ወደኛ ቢመጣ ተመኘሁ ወዲያው ፈቃደ እግዚአብሔር ቢሆን ቢሳካ ትችላለህ ብየ ጠይቄው ፈቃደኛ መሆኑን ተረደረቻለሁ ይህ ሰባኬ ወንጌል በተለያዩ የሀገሪቱ ቋንቋ ስብከተ ወንጌል የሚሰጥ ገንዘብ በማሰበሳብ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ የአደረገ ለዚህ ተሰጥኦ የአለው ነው ሊቀ ጳጳሱን ጠይቄያቸው ፈቃደኛ ሆነዋል፡፡ የገንዘብ ማሰባሰቡ ቀጠለ ታቦታቱ ውጪ ቆመው ቅደሴ ተጀመረ ፍሬ ቅዳሴ ላይ ታቦታቱ ገቡ፡፡

ይህ አሠራር የቤተ ክርስቲያናችንን ቀኖና ይቃወማል ይሁዳን ያስመስላል። አብዛኛዎቹ የተጎዘንባቸው አብያተ ክርስቲያናትም ሆኑ ገዳማት ያለገንዘብ ሌላ ጥያቄ አልነበረም የተለያየ ችግር ስለአለባቸው አብያተ ክርስቲያናቱ በዙርያቸው የሚበልጡት የሚያለሙት ቦታ አላቸው ግን ወደዚያ እንዲመለከቱ እራሳቸውን ረድተው ሌላውን መርዳት የሚችሉበት የአመለከታቸው የለም እነሱም ፍላጎቱ የአላቸው አይመስልም የሚያቻል ቢሆን በወጪ የአለች ቤተ ክርስቲያን የሥርቶ ማሰየት ማዕከል በአንድ በተወሰነ ቦታ ለመጀመርያ ጊዜ አድርጋ ከዚያ በየክፍላተ ሀገሩ በማቋቋም ድጋፍ ብትሰጥ በቀላሉ ችግሩ ይቃለላል ብየ አምናለሁ እያንዳዱ በግል የሚደረገው እርዳታ ወደ ማኅበር ቢለወጥና በእቅድና በፕሮግራም ቢሠራ እራሳቸውን ለማስቻል ከአሃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ለማስተካከል ከሦስት ዓመታት እስከ አምስት ዓመታት በቂ እንደሆነ እገምታለሁ።

ከቅዳሴ በኋላ ጉዞ ወደ ሚዘን ተፈሪ ተደረገ በምሽት ደረሰን።ሚዛን ተፈሪ በ1992 ዓም በአቡነ እስጢፋኖስ የተመሠረተ ሲሆን የሚኖሩትም መነኮሰይያት ናቸው መነኮሰይያቱ ምንም ከቤተ ክርሰቲያንም ሆነ ከሌላም በጀት እንደሌላቸው በራሳቸው ጥረት ብቻ የሚኖሩ መሆኑን ገለጻ የአደርገውልናል። ከሚያመርቷቸውም መካከል አንዱ ዳቦ በመጋገር ሲሆን ይህንን ሥራ ለማስፋትና ለሆስፒታልና ለመሰሉት ድርጅቶች በኮንትራት መልክ ለመስጠት መብራት የሚኖርው በተወሰኑ ቀናት ስለሚሆን ይህ ችግር ሆኖብናል ጀነሬተር ቢያገኙ ችግራቸው የሚቃለል እንደሆነ ገልጸውልናል። ሌላው ደግሞ ጥሩ ውጤት የአሳየው ህፃናትን ማስተማር ሲሆን የሚያስተምሩበት ቦታ ተከራይተው በመሆኑ ከፈላጊው ብዛት ሁሉንም ለማስተናገድ የቦታ ጥበት ስለገጠማቸው ይህንኑ ችግር ለመንግሥት አቅርበው ለዚያ የሚሆን ተስማሚ መሐል ከተማ ላይ ሠፊ ቦታ እንደሰጣቸውና ከገንዘብ አቅም የተነሳ መሬቱን ሊጠቀሙበት እንዳልቻሉና መንግሥትም ሲሰጠን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሠርተን እንድን ገለገልበት ነበር ስለአልሆነልን የተሰጠን መሬት ለሌላ ባለገንዘብ እንዳይስጥባቸው ሥጋታቸውን እንባ በተቀላቀለበት ትከዜ በመግለጽ ደረጃ በደረጃ ለማሰራት የአዘጋጁትን ፕላን ስጥተውናል።ሌላው ገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ በገዛልን ቦታ ላይ ለከብት እርባታ እንዲውል ሙከራ አድርገን የከብት መኖ ከማጣት የተነሳ የነበሩንን ከብቶች እየሸጥን ነው ቦታው ሳይገዛልን በፊት የቡና የማንጎ የመሳሰሉ አትክልቶች ስለነበሩ እነዚያን የበለጠ በማሳደግ መጠነኛ ገቢ እንደሚያገኙ አስረድተውናል።

በውነት ይህ የሴቶች ገዳም በማንኛውም የተዋጎዶ ልጅ በየትኛም አቅጣጫ በውስጥ በወጪ የአሉ ሊረዱት ይገባል እምነት የሚጣልባቸው የማያሳፍሩ መነኮሳይያት ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተመርቀው የወጡ ስለአሉበት በዚህ የወጣትነት ዘመን ለሥጋ የሚያስፈልገውን ምቾትና የዓለምን ጣዕም ንቀው የገቡ በመሆናቸው የዓይን ምሥክርነቴ አረጋግጣለሁ። እነዚህንም የአሜሪካዋ ቤተ ክርስቲያን ለማቋቋ ጊዜ እንደ ማይወስድ ተረድቻለሁ እነሱ ዘንድ ጉለበቱ ውቀቱና የመሥራትፍላጎቱና ቦታው አላቸው ቦታው ማቋቋሚያ ገንዘብና አይዟችሁ የሚላቸው ብቻ ነው የሚያስፈልጋቸው ይህንኑ ድጋፍ ሽተው ወደቤተ ክህነቱ በሄዱበት ወቅት «እናንተን አንረዳም እናንተ ጴንጤ ናችሁ» እንደተባሉና በዚሁ የተነሳ ከመነኮሳይያቱ አንዷ ጴጤስ አይደለንም ብለው ከቁጥጥር ወጪ አንደሆኑና እየጮኹ ከባለሥልጣኑ ፊት ወጥተው እንደሄዱ ተስፋ እዳስቆረጣቸው ለመረዳት ችለናል።

ከሚዘን ተፈሪ መልስ ጉዞ መካከል በአውቶቢስ የተሳፈሩት ቀጥታ ወደ ጅማ ሲያመሩ እኔ ከጋቤላው ሀገረ ስብከት ከመጋቤ አእላፍ  ተክለ ሃይማኖት ጋር ገዳመ ቆሮቶስ ተብሎ የተሰየመ የአባታችን የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ስም ገዳሙ የተገደመ በአጠገቡ በጣም የሚያስደስት የዙቃላን ሐይቅ የመሰለ ገዳም ገብኝተናል በዚያ የአሉ አራት የወንድ መነኮሳት አንድ ሴት መነኩሲት አግኝተናል በግቢው የቡናው የሽንከራውና የሙዙ የፓፓየው አትክልት ሲያስደስት ገነትን ያስታውሳል እነዚህ አራት መነኮሳት ምንም ከፍያ የሌላቸው የጎደሬ ሥር ብቻ በመብላት የሚኖሩ መሆኑን ተረድቻለሁ የእንጀራና ወጥ ለትንሳኤ እንኳን ማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ ላይ እንዳሉ ተመልክቻለሁ አንዲት መንኩሲት ስለነበሩ ለመሆኑ ለምን ወደዚህ ገዳም መጡ ብዬ ስጠይቃቸው«ቢከፋኝ አባቴ» ሲሉ መልሰውልኛል መኖርያቸውን በተመለከተ የወፍ ጎጆ የመሳሰሉ ከእንስሳት ከአራዊት በአነሰ ሁኔታ የሚኖሩ መሁኑን የዓይን ምሥክር ነኝ።የክፍሉን ሥራ አስካጅ መጋቤ አእላፍ አባተክለ ሃይማኖትን  ለምንድ ነው እነዚህን የመሳሰሉ ገዳማት ቤተ ክህነቱ የማይረዳቸው እንዲቋቋሙ የማያደርጋቸው?ብየ ስጠይቃቸው«ተከድኖ ይብሰል አባቴ»በማለት ከመናገር ተቆጥበዋል ለመሆኑ ይህንን የሚረዱ ምዕመናን ከተገኙ በወር ምንያህል ለየአንዳዳቸው ቢከፈላችው ይበቃል ብዬ ለጠየቅኋቸው ሲመልሱ ከመቶ ሃምሳ አስከ ሁለት መቶ ብር በቂ ነው ሲሉ መልሰውልኛል ለአራት መነኮሳት በመቶ ሃምሳ ቢያዝ በወር ስድስት መቶ በሁለት መቶ ቢታሰብ

ሰምንት መቶ እንግዲህ ይህንን ሪፖርት የሰማችሁ የአነበባችሁ እንዚህን ድምፀ አራዊቱን ፀብአ አጋንንቱን ታገሰው የሚኖሩ አባቶችን በመርዳት አንዱንየቤተ ክርስቲያናችሁን ቀዳዳ እንደትሸፍኑ በእግዚአብሔር ስም አሳስባለሁ።ወደ ኢትዮጵያ በዘለቃችሁም ጊዜ እንድትጎበኞቸው እለማናለሁ እንዳየበተኑ ድረሱላቸው።

የቤተ ክርስቲያናችን ችግር ብዙ ውስበስብም ነው። አራተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት «እያላት የሌላት ቤተ ክርስቲያን»ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው በአንድ ስብሰባ ላይ የገለጹት ትዝ አለኝ ከአህት አብያተ ክርስቲያናት በርካታ አባላት ብዛት የአላት የእኛ ቤተ ክርሰቲያን ናት ። ችግረኛዋ ደግሞ የእኛው ቤተ ክርስቲያን ናት እኔ በዚህ ጉብኝቴ የደረስኩባቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሁሉ የሰማሁት ልመና የአየሁት ችግር ብቻ ነው ይህን ችግሩን በቀላሉና በተወሰኑ ጊዜያት መፍታት በአሜሪካ የሚኖሩ ክርስቲያኖች በተቀናጀና በተባበረ ኃይል ተነስተው ቢሠሩ በስደት የአሉ ፓትርያሪኩም ሆኑ ሊቃነ ጳጳሳቱ ሀገር ቤት ከአሉት አባቶች ጋር እርቅ ቢፈጥሩና የቀደሙ የአባቶቻችንን ሕይወት ቢኖሩ አሁን የምናው የአብያተ ክርስቲያናቱና የገዳማቱ ችግር ተጠቅሎ እንጦርጦስ ይወርዳል ብየ አምናለሁ ይህ አንድነት እንዲመጣ አበክሮ መጸለይ ያስፈልጋል።

ከዚያም ወደ ጅማ አመራን ጅማ ወደ ስድሰት ሰዓት አካባቢ ደርሰን በመንበረ ጵጵስናው ምሳ በልተን እረፍት ከአደረግን በኋላ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ ጥምቀት የሚከበርበትን በ1997 ዓ.ም በ40 ቀን የተሠራውን የዑራኤል ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በዘመናዊ መልክ የተሠሩትን የካህናት ማሰልጠኛ እንድንጎበኝ አድርገዋል።በውነት ሜዳው የጃን ሜድን የሚመስል በጣም የሚያስደስት ሥፍራ ነው ይህንን የምታዩትን ሜዳ በ1997 ዓ.ም ነው ካርታ እንዲኖረው የአደረግነው የዘመኑ ሀብታሞች እጅ ሊያደረጉት አሰፍስፈው ለእኛ የመሆኑ አጠራጣሪ ነበር በእግዚአብሔር ቸርነት በብዙ ትግል ልንረከበው ችለናል ለዚህም ይህንን ቦታ እጃችን ልናገባ ዋና ማስረጃ የሆነን ደጃዝማች ፀሐዩ እንቆዕ ሥላሴ የአቆሙት መስቀል እንደሆነ ጥምቀተ ባሕሩ የሚፈጸምበትን መስቀሉን አሳይተውናል።ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል ይህ ሠፊ ቦታ ዙርያውን የሆነ ነገር ከአላደረግንበት እንዳይወሰድ እንሰጋለን ብለዋል ምን ያሰባችሁት እቅድ አለ ተብለው ለተጠየቁት ሲመልሱ ከአቅም እጥረት ነው እንጂ ብዙ የሚሠሩ አሉ

1. የዩነቨርሲቲ ተማሪዎች በትምህርት ጊዜ ጥናታቸውን ሲያጠኑ በዚህ ሥፍራ ነው ፈሰው የሚታዩት ከአፍሪካ የመጀመርያ እንደሆነ የሚነገርለት ዩንቨርስቲ እዚህ በአጠገባችን ነው የአለው ለተማሪዎቹም ሆነ ለአንባብያን የሚሆን ቤተ መጻሕፍት ቢቋቋም

2. ተማሪው እዚሁ ጥናቱን ሲያጠና ቁርስ ሻይ ቢያስፈልገው ርቆ ሳይሄድ እዚያው በቅርቡ እንዲያገኝ እንደ ሻይ ቤት ያለ ቢሠራ

3. የባለሞያ ኃይል ስለአለን በርካታ የቤተ ክርስቲያን ልጆች የጤና ባለሞያዎች ዶክተሮች ነርሶች ዲቁና ቅስና እየተቀበሉ በእረፍት ጊዜያቸው የቤተ ክርስቲያናችንን ሙያ እያጠኑ ስለሆነ በሽፍት ነፃ አገልግሎት የሚሰጡ ምሁራን ስለአሉ አንድ የተማላ ክሊኒክ(መለስተኛ ሆስፒታል)ቢኖር ቦታውን ከመጠበቅ በአሻገር ለሀገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን እዚህ ለአለው ኅብረተ ሰብ ጠቀሚ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዚሁ መነሻነት የእኔን የግሌ ኃሣብ ተዘዋውሬ እንዳየሁት በየመንገዱ በየተወሰነ ርቀት ተጽፎ የሚታየው መካነ ኢየሱስ መሠረተ ክርስቶስ ሙሉ ወንጌል የሚል ነው የመስጊዱማ ይህ ነው አይባልም እነዚህ ሁሉ ህዝቡን የሚያጠምዱት የሚበላ የሚጠጣ የሚለበስ በመስጠት ክልኒክ ትምህርት ቤት በማነጽ ነው የእኛን የቤተ ክርስቲያን ለጆች ሊወስዱ የቻሉት በዚህ ዓመት መንግሥት በአወጣው የሕዝብ ቆጠራ ሕዝበ ክርስቲያናችን በመቶ ሰምንት ዝቅ ብሏል ተብሎ የሚነገርለት እሰከ ዛሬ በነገሥታቱ ተጠብቃ ቆይታለች ከእንግዲህ ይህ እድል አይኖርም ቤተ ክርስቲያናችን ሐዋርያት እንደመሆኗ መጠን ምዕመናን ናቸው አሥራታቸውን በማውጣት እንደሌሎች አሃት አብያተ ክርስቲያናት በምጣኔ ሀብት በምዕመናኖቿ መደገፍ አለባት ቤተ ክርስቲያንም ለልጆቿ ሥፍራ መስጠት ያስፈልጋታል፡፡በጅማ ሀገረ ስብከተ እንደ ተመለከትኩት ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ በምሳሌ የሚጠቀሱ አባት ሆነው ነው የገኘኋቸው ሐዋርያው«ወኩሉ በግዕዘ ኩሉ ተለውኩ» እንደላው ሁሉንም በየመልኩ የሚያስተናግዱ የተሰጣቸውን አደራ የሚወጡ በመሆናቸው እንዚህን ከላይ የጠቀሷቸውን ለማከናወን ፈቃደኛ የሆነ ማንኛውም በውስጥም በውጪም የሚኖር የተዋኅዶ ልጅ ሃይማኖታዊ ግዴታውን መወጣት የሚገባው ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ችግር ላይ በወደቀችበት በአሁኑ ወቅት እንደሆነ ይሰማኛል ልጅ ልጅ የሚባለው ለእናቱ በችግሯ ሲደርስ ነውና በእሳቸው በኩል የሚደረገው ስጦታ በትክክል ሥራ ላይ አውለው በተግባር የአየሁትን ምሥክርነቴን አረጋግጣለሁ፡፡

## ዘጠነኛ ቀን ረቡዕ የካቲት አራት ቀን የመልስ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ

ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ በዚህ ቀን እንደዛሬው የዛሬ ሳምንት የአቡነ ሐራ ማኅበር ልጆቻቸውን አዲስ አበባ በመገኘት እየመሩ እየአሳዩ መግለጫ እየሰጡ ጅማ እንዳደደረሱ ሁሉ አሁንም እንደዚያው አስከ ግቤ ወንዝ አድርሰው በጸሎትና ቡራኬ ሰጥተውን ተመልሰዋል፡፡በአበልቲ ኪዳንምሕረት ገዳም ትልቅ መስተንግዶና ውይይት ተደርጓል፡፡ዝርዝር ሁኔታውን በዲቢዲው ይመልከቱ፡፡

## አሥረኛ ቀን ሐሙስ የካቲት አምስት ቀን የወላይታ ጉዞ

በወላይታ ዞን የተደረገ በወ/ሮ ራኄል መኪና በአቶ ጌራ ሾፋሪነት ዮሐንሰ ቤተ ክርስቲያንና ደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ገዳም የአገልግሎት ጉብኝት ከንጋቱ ስደስት ሰዓት በመነሳት ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ደረስን አቶ ጌራና ወ/ሮ ራኄል መኩርያ መኪናዋን ለጋራዥ ለማሳየት ወደ ሰዶ ከተማ ሲያልፉ እኔ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ቀረሁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ አዲስ ህንፃ እየተሠራ ነው፡፡ሲሆን ታቦቱ የመጣው በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ከሰላሌ አውራጃ አድስጌ ወረዳ ከወዴሶ እንደመጣ የነበረበት ዘመን በትከክል የተጻፈ ነገር ባይኖርም በቅብብሎሽ ከሽማግሌዎች እንደነገሩኝ ደብረ ሊባኖስ ገዳም በደባልነት እንደነበርና ተንባላት ገዳሙን ሲወሩ ታበቦታቱን ለማትረፍ ካህናት ጠላት ለመድረስ በማይመችው ቆላማ ሥፍራ ይዘው በየሥፍራው ሲበተኑ በዚህ ምክንያት አድስጌ ወዴሶ ዮሐንስ እንደተከለና ይህ ታቦት ከዚያ ወላይታን ለማቅናትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት ወደዚህ ሲመጡ መምህር አብየነህ ይዘው እንደመጡ የሚናገሩ አሉ በሌላ በኩል ደግሞ አብየነህ ሀገር ለማቅናት ሃይማኖትን ለማስፋፋት ወደ ዳር ሀገር ተብሎ ሲጣራ ወደ ነበረው ወላይታ ሲመጡ እሳቸው እራሳቸው አስቀርፀውና አስባርከው ይዘው እንደመጡ ግምት የሚሰጡ አሉ ይህ ሁሉ በትክክል የተጻፈ ነገረ ባለመኖሩ ነው የብራና መጻሕፍቶቻችን ብዙዎቹ ማን እንደጻፋቸው መቼ እንደተጻፉ የሚያመለክት ምንም ፍንጭ የሌላቸው አሉ፡፡ ይህም እንደዚሁ ሁኔታ ሲያመች ዘመናትን በሚያረጋግጥ መሠርያ ለማወቅ የሚቻልበትን መንገድ ወደ ፊት ሊሠራ ይችላል፡፡ቤተ ክርስቲያኑ ምንም ገቢ የሌለው የሚያስገለግሉና የሚያገለግሉትም እንዲሁም ህንጻ ቤተ ክርስቲያኑን እንዲገነባ እያደረጉ የአሉት ጠቂት የመምህር አብየነህ ዘሮች

ናቸው።እንሱም ታሪክን ለመጠበቅ ነው እንጂ ምንም የሌላቸው ከእጅ ወደ አፍ እንደሆኑ ለማወቅ ችያለሁ። ይህ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሊረዱ ከሚገባቸው አንዱ ነው። መናፍቃን የነገሡበት በርካታ የኦርቶ ዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማንያን እጃቸውን የሰጡበት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በእነሱ የተተኩበት ፈታኝ ሥፍራ እንደሆነ ተረድቻለሁ።የአክራሪው እስልምናም ቢሆን በዚያው መጠን ተጽእኖ እያደረገ ነው።የተጀመረውን ህንፃ ቤተ ክርስቲያን ለማስፈጸምና ህፃናት የሚማሩበት ትምህርት ቤት እንዲኖር ማድረጉ አማራጭ የሌለው ነገር እንደሆነ ተረድቻለሁ መናፍቃኑ የኦርቶደክሳውያን ልጆች የወሰድዋቸው አንደኛው በዚህ መንገድ ነውና።

እንደተነገረኝ በአሁኑ ሰዓት የዞኑ ኃላፊዎች በጠቅላላው ወላጆቻቸው ኦርቶ ዶክሳውያን የነበሩ እነሱ ግን ፕሮቴስታንቶች ናቸው ምክንያቱ በእነሱ ትምህርት ቤት ገብተው ስለተማሩ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል። የወደፊት የቤተ ክርስቲያናችን ሥራ መሆን የሚገባው ለአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ልሔምና ደጀ ሰላም እንሚያስፍልግ ሁሉ ትምህርት ቤት መኖር ግዴታ እንደሆነ አደርጎ መወሰድ እንዳለበት የእምነቱ ተከታይ ሁሉ ሊገነዘብ ይገባል ከዚህ በቀር ቤተ ክርስቲያኗን የሚያድን የሚታደግ ነገር እንደሌለ በዚህ አገልግሎታዊ ጉዞዬ የበለጠ ለማወቅ ችያለሁ።

ከዚህ ከዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን የጻድቁ አባታችን አቡ ተከለ ሃይማኖት ገዳም ተጓዝን ገዳሙ ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን ታሪካዊ ና ጥንታዊ ነው።አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትልቅ ተጋድሎ የአደረጉበት ለወላይታ ሕዝብ ውለታ የአደረጉበት ሥፍራ ነው በተለይም አራተኛው ፓትርያሪክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አባ መልአኩ እየተባሉ ለወላይታ ሕዝብ ከስድሳ የበለጡ አብያተ ክርስቲያናት በማሳነጽ ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም ትልቅ ሥራ ሠርተዋል።የብህትውና ሥፍራቸውም በዚሁ ገዳም ነበር።ቤተ ክርስቲያኑን የጥንቱ እንደነበረ አለ አዲስ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ መሠረት ተጥሎ በመሠራት ላይ ይገኛል። አባ መልአኩ (ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት)ገድል ሲፈጽሙበት የኖሩበት ሥፍራ በሚገባ በአለመጠበቁ እየፈራረሰ ይገኛል። ይህም የሚያሳዝን ነው። እንዲዚህ የአለውን ታሪካዊ ሥፍራ መጠበቅ አለበት ከክፍሉ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኒቆዲሞስ ጋራም ለመገናኘት ችያለሁ ብፁዕ አባታችን በ71 ዓ.ም ሊቀ ሥልጣናት በነበሩ ጌዜ አሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት በአንድ ጊዜ

በምትሾበት ወቅት በአብዮቱ ግርግር ወቅት አብረን ሠርተን ስለነበር ያን አውስተው ብፁዕ አባታችን የአለፈውን ትዝታ አውስተው ከአጨዋወቱኝ በኋላ ከርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያ ለተራበው ህዝብተብሎ የተሰበሰበው ገንዘብ በወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ አማካይነት እርዳታው የተሰጠው በዚህ አካባቢ መሆኑን ሲያስረዱኝ በዚያን ወቅት የአካባቢው ሕዝብ ይህንን እርዳታ ማግኘቱ ብዙዎቹን ከሞት የአተረፈ እርዳታ እንደሆነ አስረድተውኛል እንዳጋጣሚ እርዳታው ከደረሳቸው ከቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ተጠልለው የነበሩትን አግኝቼ ሳነጋግራቸው ሰማዩ ተደፍቶብን ተስፋ ቆርጠን ለሞት እየተዘጋጀን በአለንበት ወቅት ነው እግዚአብሔር የላከልን እስከአሁን ያችን እየቆጠብን እየተመገብን ነው የአለነው ማለቂያው እየደረስ ስለሆነ ምን እንሆን ይሆን እያልን የአለንበት ወቅት ነው ሲሉ ችግራቸውን ገልጸዋል።

የጥንቱ ባህታዊ አባ መልአኩ የኋላው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የጸሎት መኖር ቤታቸው መፍረስ ችላ መባል አንስቼ ብፁዕነታቸውን ጠይቄ የሰጡኝ በእርግጥ እኝህ ታላቅ አባት ታላቅ ሥራ የሠሩበት ቦታ በአግባብ ተይዞ ለዝክረ ነገር መጠበቅ ጎብኚዎችን የሚስብ ለገዳሙም ገቢ የሚያስገባ ነበር የግብፁን አቡነ ቄርሎስን አውስተው እንደምሳሌ አደረገው በማቅረብ አስፈላገነቱን አረጋግጠው ያን እንዳናደርግ የሚከለክለን የአቀም ማጣት ነው ሲሉ አስምረውበታል።

በርግጥም ብዙ ነገር ሊሠራ የሚችለው የአካባቢ ነዋሪ ነበር ነዋሪው ሕዝብ እንኳን የዚህን ዓይነት ሥራ ሊሠራ ቀርቶ ለቁመተ ሥጋ ያህል እረሱን መጠበቅ ባማይችለበት ሁኔታላይ ነው የአለው በውነት ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በአሜሪካ የአለቸው ቤተ ክርስቲያን በኅብረት ብትሠራ ታሪካዊ ቦታዎችን መጠበቅና ማስጠበቅ በዚህም አማካይነት ለቤተ ክርስቲያን ልጆች የሥራ መሥክ መፍጠር የቤተ ክርስቲያንን ገቢ በቱሪዝም ማሳደግ የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊነትና ብሔራዊትነቷን እንደያዘች እንድትቆይ ማድረግ ይቻላል። በውጪ የአለን ካህናትና ምዕመናን እንደ ዮሴፍ በውጪ ዓለም የአከበረን ለቤተ ክርስቲያናችንና ለሀገራችን እንድንደርስ በመሆኑ እስከአሁንም የተደረገው በቀላል የሚገመት አይደለም ለብዙዎች ሕይወት መትረፍ ምክንያት አድርጎናልና አሁንም ከዚህ የበለጠ ይጠበቅብናልና ይታሰብበት እላለሁ።

**<u>አሥራ አንደኛ ቀን ዓርብ የካቲት ሰድስት ቀን 2001 ዓ.ም</u>**

በዚህ ዕለት በአዲስ አበባ አካባቢ የአሉትን አብያተ ክርስቲያናትንና ህመምተኞችን መጎብኘት ቀሪውን ጊዜ የኬንያን ጉዞ ማመቻቸት

## አሥራ ሁለተኛ ቀን ቅዳሜ የካቲት ሰባት ቀን 2001

በዚህ ዕለት ከአቶ ፍሬው ቡልቡላ ጋር በመሆን ለቤተ ክርስቲያናችን የሚሠራውን መጎናጸፍያ የሚሠራበት ቦታዎችን በመዘዋወር መምረጥ የአደረግንበት ነው ቀደም ሲል አቶ አድማሱን ወክሎ የሚሠራው አቶ አለማየሁ ለአንድ መጎናጸፊያ ከዘጠና ሺ የኢትዮጵያ ብር የበለጠ ስለጠየቀ ከሌላው ከዓየነው ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ መጨመሩን ያሳያል ሄደን እንደጠየቅነው የሚሠራበት ዕቃዎች ተገዝተው ሥራው እንዳልተጀመረ በመግለጽ ቀብድም ቢሰጥህ ሥራውን እስከምናዝህ ይቆይ ዋጋህንም ቀንስ ብለነው ሄደናል፡፡ እረፍት የተደረገበት ቀን ነበር፡፡በማግሥቱም ጉዞ ወደ ኬንያ፡፡

## አሥራ ሦስተኛ ቀን እሁድ የካቲት  ስምንት ቀን 2001 ዓ.ም

በዚህ ዕለት ከጧቱ አንድ ሰዓት በመነሳት ወደ ቦሌ አየር መንገድ መሄድ በዚያም አስፈላጊው የጉዞ ዝግጅት እንደበቃ አየሩ ልክ በአራት ሰዓት ተነስቶ ናይሮቢ ከቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት ደረስን ሁለት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች በታከሲ ተቀብለው ምሳ ወደሚበላበት የኢትዮጵያ ምግብ ቤት ወሰዱን ከዚያ ከአንደኛው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ጋር በመሆን ናይሮቢ ሳናድር ወደ ካኩማ ስደተኞች የሚወስደውን አውቶቢስ ለመያዝ በታክሲ አውቶቢስ ጣቢያ ደረስን አውቶቢሱ አሁን በቶሎ ይሄዳል ግቡ ተባልን ገባን ከአሁን አሁን ይሄዳልን ስንል ከቀኑ ስምንት ሰዓት የገባን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ለመሄድ ሲንቀሳቀስ ሄዶ ሄዶ ሲመለስ ከግማሽሰዓት በላይ ከተነቆራጠጠ በኋላ ጉዞ ጀመረ መንገዱ አስፋልትም ቢሆን ብልሽት የበዛበት ጥገና የአልተደረገለት በመሆኑ ብድግ ቁጭ ማለት ነበረበት፡፡ ከዚያ ሌላ አውቶቢስ የምንዘወርበት ከተማ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ደረስን ሌላው አውቶቢስ ላይ ተሰፈርን እዚያ ላይ ተቀምጠን ይነሳል እያልን ስንጠብቅ ከቀኑ ሰድስት ሰዓት ሆነ የፀሐዩ ግለት የቧራው ብዛት ይህ ነው አይባልም ይህ በዚህ እያለ ዘጠኝ ሰዓታት ያህል በመኪናው ውስጥ ስንጠብቅ የቆየነው ከንቱ ሆኖ ይህ አይሄድም ሌላው ላይ ተሰፈሩ የሚል ትእዛዝ መጣ እቃ ተሸክሞ የነበረው ትንንቅ ቀላል አልነበረም ሌባም እንዳይመነትፍ ሥጋት ነበር ከእኛ ጋር በተጓዛው በረዳታችን በአበበ

ብርታት ቦታ አገኘን ሰኞ አሥራ አራተኛ ቀን የካቲት ዘጠኝ ቀን ከእኩለ ቀን በኋላ ጉዞ ወደ ካኩማ ተጀመረ ጭው የአለ በርሃ የፀሐዩ ሙቀት ግምት የሚሰጠው አይደለም የመንገዱ ወጣ ገባነት ወደ ሰማይ አንጥሮ ወደ ምድር ሲወረውር ሁሉም እስፖርት የሚሠራ ይመስላል በመንገዱ በርሃማነት የፀጥታ ሥጋት ስለአለ ሁለት መሣርያ የያዙ ወታደሮችም ነበሩ በዚህ ዓይነት ቀኑን ፈጽመን ሌሊቱንም ጉዞ በነበረው ሁኔታ ቀጠልን ለማክሰኞ አጥቢያ ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ካኩማ ከተማ ደረስን ከውቶቢሱ ስንወርድ ነገ ጣቢያ እንዳንገናኝ ጥንቃቄ እንደናደርግ ማሳሰቢያ ሰጥተውን ከሰዎቻችን ጋር አስከምንገናኝ ጠብቀውን ሄደዋል፡፡የቤተ ክርስቲያኑ ኃላፊ ቀሲስ ዓለሙ ማሞ የሰበካ ጉባዔ አባላት አቶ በፈቃዱና አቶ አባተ ተቀብለው ወደ ተያዘለን ማረፍያ አስገብተውን እረፍት አድርገናል፡፡

## <u>አሥራ አምስተኛው ቀን ማክሰኞ የካቲት አሥር ቀን 2001</u>

ጧት ማክሰኞ በካኩማ ዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በመገኘት የነግህ ጸሎት አደረስን ገና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲኬድ ህንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ሲታይ እዚህ በርሃ የዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን ሲታይ የሚያስደነግጥ ነው በመጀመርያ ሳየው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ወይም የሌሎች ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያን ነው የመሰለኝ እንጂ የእኛ ነው ብዬ አልገመትኩም የት ነው የእናንተ ከዚህ ወዴት ነው? ብላ ራኄል መኩርያ ስትጠይቅ ይሄ እኮ ነው ብለው ሲመልሱላት በጣም ተደነቅን እግዚአብሔርን አመሰገንን በዚያው የነግህ ጸሎታችንን አደረስን ከዚያ ስንወጣ የግቢው ሥፋት ይህ ነው አይባልም በመጀመርያ መሠረት የተጣለበትን አምስት መቶ አስኪር ካሪ ነበር የሀገሩ ተወላጅ እምነቱን የተቀበለው ችፍ ዮሴፍ የሰጠው በኋላ ገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የወገንነፍስ አድን ኮሚቴ ገንዘብ ልኮ እንዲገዛ ያደረገውና መንግሥትም ትጋታቸውን ዓይቶ በነጻ እንደጨመረላቸው መረዳት ችለናል፡፡በዚህ በበርሃ በስደተኛ አቅም እንዲህ የአለ ቤተ ክርስቲያን ከተሠራ እኛማ ምን ዓይነት በሠራን ነበር የሚል መንፈሳዊ ቅናት ተሰማኝ ቤቱን የሚሠራው ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር እንደሆነም ለመረዳት እንድችል አደርጎኛል፡፡

ከዚያም በኋላ ችፍ ዮሴፍ ታመው እቤት መሆናቸውን ነገረውን ለመጠየቅና ሰላም ለማለት ወደ መኖርያ ቤታቸው አመራን እንደ ደረስን ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመሆን አገኘናቸው ስለአመጣጣችን ስለህመማቸው

ከተነጋገርን በኋላ ምሳ ከእሳቸው ጋር ተመግበን ማታ የሀገሩ ተወላጆች የኮሚቴ አባላት በችፉ ቤት እንዲገኙ እንዲደረግ ቀጠሮ ተይዞ በዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እንድንገኝላቸው ጋብዘውን እንኳን ከእነሱ ጎንደር ሄደው ሞያውን ከአጠኑት ያሬዳውያን በአለነሰ ሁኔታ የቅዱስ ያሬድን ዝማሬ አቅርበውልናል፡፡የድምፃቸው አሰባበር የመቋሚያ አያያዝና የፀናፅል አጣጣላቸው በጣም የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ነበር እግዚአብሔር የፈለገውን ማስነሳት እንደሚችል ልንገነዘብ ችለናል፡፡ዓይቶ ለመፍረድና እግዚአብሔርን ለማመስገን ዲቪዲውን ይመልከቱ፡፡ በችፉ ቤት ሊደረግ የተያዘው የማታው ቀጠሮ ለማግሥቱ ረቡዕ ተላለፈ እኛም ወደ ማረፍያችን ገባን፡፡

## <u>*አሥራ ሰድስተኛው ቀን ረቡዕ የካቲት አሥራ አንድ ቀን 2001*</u>

በዚህ ዕለት ስደተኞች የሚኖሩበት የስደተኞች ዓለም ወደ ሆነው ሥፍራ ተጓዝን ተኪዶ የማያልቅ ትልቅ ከተማ ነው በዚያም ምስካዬ ስዱዳን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን የሚገኝበት ነው፡፡እነዚህ ሁለት ህንፃ አብያተ ክርስቲያናት የተሠሩት በስደተኞች የኦርቶዶክስ ተዋኅዶ እምነት ተከታዮች ነው፡፡አብያተ ክርስቲያናቱ የታነፁበት በአቀማመጥ ከፍ የአለ ቦታ በዙርያው አበው ካህናት መረፍያ የተሰራበት አዳራሽ ጽ/ቤት የተሠራበት ግቢው ሥፋት የአለው በኬንያ ኅብረተ ሰብ የማይፈቀድና በሀገሩ ደንብ የሌለ ለኢትዮጵያውያን ስደተኞች ብቻ ሲሞቱ የሚቀበሩበት ሥፍራ እንደ ተ ፈቀደላቸውና የብዙዎች ኢትዮጵያውያን አስከሬን የአረፈበትን ለማየት ችለናል፡፡

በቅድምያ ስደተኛውንና መንንግሥትን የሚወክል ባለሥልጣን ወደ ካፑ ለመግባት ፈቃድ ማግኘት ስለነበረብን ከቺፉ ጋር በመሆን ወደ ጽ/ቤቱ አመራን የክፍሉ ኃለፊ በአክብሮት ተቀብሎ እዚህ አካባቢ እስከምንቆይ እንደልባችን እንድንወጣ እንድንገባ ፈቀደልን በዚሁ ወደ ቤተ ክርስቲያናቱ በመሄድ ተሳልመን በውስጥም በወጪም የአለወን ሁሉ አንድ በአንድ ተመለከትን የእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን ከመድኃኔ ዓለም አዲስ ሆኖ ይታያል በቅርብ ጊዜ እዚህ የነበረ አቶ በጋሻው ስዕለት ተስሎ ስለነበር ከአሥር ሺ ዶላር በላይ ልኮ የተሠራ እንደሆነ ገለጻ ተደርጎልናል፡፡የጥንቷ በስደተኞች የተሠራችው ቤተ ክርስቲያን ለዝክረ ነገር ተቀምጣለች የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ከበርሃማነቱ ጽናት ከነፋሱ ብዛት እንደሆነ አለውቅም የዛሬ አምስት ዓመት እዚህ በነበርኩ

ጊዜ ከአየሁት የውስጡ ኮርኒስ ተለያይቶ ጣርያውም እንደሚያፈስ ተመልክቻለሁ ቀሲስም ለዘህ ለዓምስት ዓመታት ተኩረት የሰጠነው ለገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ስለነበር ከእንግዲህ ወደዚህ እንዞራለን ብለዋል በዚህ አጋጣሚ ወገኖቻችንን እናሳስባለን ቆርቆሮ ብቻ መለወጥ እንደለበት ነው ገለጻ የአደረጉለን የኢትዮጵያውያኑን መካነ መቃብር ስንጎበኝ አዲስ መቃብር ተመለከትን ይህ የምታዩት አዲስ መቃብር አንዲት እህታችን መውለጃዋ ጊዜ ደርሶ አንቡላንስ በጊዜው በአለመድረሱ የተነሳ ክሊኒክ የሚያደርስ መኪና በመታጣቱ የእርሷም የህፃኑ ሕይወት እንዳለፈ አስረደተውናል ባለቤቷና ህፃናት ልጆቿ ወደ አሉበት ሥፍራ በመደረስ ባለቤቷን አጽናንተን ለጆቿን አረጋግተናል፡፡
ይህን ችግር የተመለከተችና የሰማች እህታችን ወ/ሮ ራኄል መኩርያ ይህንን ለመሳሰለው ችግር ይረዳ ዘንድ በታክሲነት የምታገለግል ሦስት እግር መኪና ገዝታ ለቤተ ክርስቲያኑ ለማበርከት ቃል ገብታለች፡፡

ከዚህ በኋላ ከአምስት ዓመታት በፊት በገዳመ ተክለ ሃይማኖት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አሳሳቢነት ከርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የተሰበሰበውን ገንዘብ ቋሚ ነገር ላይ ለማዋል ቤተ ክርስቲያኑንና ማኅበሩን በመወከል በሥፍራው በመገኘት ጀነሬተር(የኤሌትሪክ ማመንጫ)መሳርያ ቢገዛለቸው ያን ለከተማው በማከራየት ለቤተ ክርስቲያኑ የገቢ ምንጭ የሚያስገኝ መሆኑ ታምኖበት ከአሥር ሺ ዶላር በላይ የፈጀውን መሣርያውን እንቅስቃሴውንና ቤቱን ተመልከተናል፡፡በወቅቱ ጥሩ ገቢ እንዳሰገኘላቸውም በተሰጠን ሪፖርት ለማወቅ ችለናል በዚህ በኩል አያያዛቸውና አሠራራቸው የሚደነቅ መሆኑን የዓይን ምሥክር በመሆን በማየታችን በአሠራራቸው ተደስተናል ሪፖረታቸውም ከዚህ ጋር ተያይዟል፡፡

በጊዜ ብዛት የተነሳ የመሣርያው አንዳድ ክፍሎች መለወጥ ስለአለባቸው ወጪም እንዳስወጣቸው ገልጸዋል አሁንም ከአምሳ ሺ ሽልንግ የበለጠ የሚያስወጣ እንደሆነም ጨምረው አስረደተዋል፡፡

ከዚያም የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን እንደ ጸሎት ቤት የሚገለገሉበትን የቱርከና ብሔረ ሰብ በብዛት የሚኖርበትን አካባቢ ተመልክተናል ህፃናቱም በብዛት ተሰብስበው አግኝተናቸዋል፡፡ መዝሙርም ዘምረውልናል ብዙ እርዳታም እንደሚያስፈልጋቸው ተረድተናል ግን ከአቅማችን አንጻር ምንም ማድረግ በአለመቻላችን የአለንን ቸረን እያዘንን ተመልሰናል፡፡

ሐዋርያዊ አገለግሎት ለዚህ ብሔረ ሰብ ያስፈልጋል«መነ እፌኑ ኀበ ሕዝብዩ»ሆነና ሁሉም ክብሩን እራሱን ድሎቱን ስለወደደ እንደዚህ ወደ አለው ሕዝብ መድረስ አልተቻለም ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን የወንጌል አገልግሎት ሳይቋረጥ ተካሄዶ ቢሆን አፍሪካ በሙሉ የክርስትናው ባለቤት በሆነ ነበር፡፡አሁንም ማን ያውቃል ከሁለት ሺ በላይ የቱርካና ተወላጆችን ወደ ኦርቶዶክሳዊት ተወኀዶ እምነት እንዲገቡ ያደረገ ሐዋርያ መላክ ይሰነዋል አልልም ያስነሳል ብዬ አምናለሁ፡፡«ሰአልዎ እንከ ለባለማዕረር» ተብለናልና የመከሩን ባለቤት እንጠይቅ፡፡

ከዚያም ወደ መረፍያችን ተመለሰን ምሳ በልተን ንዳድ ፀሐዩ እስከሚቀነስ በማረፍያችን አሳለፈን ጥላ ሲውርድ ወደ ማታ ወደ ችፉ ቤት ስብሰባ ተደረገ የሀገሩ ተወላጆችና ኢትዮጵያውያን የኮሚቴ አባላት ተገኝተዋል ስብሰባው በጸሎት ተጀመረ አስከ አሁን የአለውን እንቅስቃሴ በጽሑፍ እንዲቀርበልን ጠየቅን ፀሐፊው ከሥራ ወደዚህ እንደመጣና ሪፖርቱ ከአሱ ጋር እንደሌለ አስረድቶ በማግስቱ ሐሙስ እንደሚያቀርብ ቃል ገብቶ ለአሁኑ በአለብን ችግር ላይ እናተኩር በሚለው ተስማምተን የአለው ችግር ተገልጾልናል፡፡

በዕለቱ ቃለ ጉባኤው ውስጥ ስለሰፈረ ከዚህ ጋር ተያይዟል፡፡ከችግሩ አንዱ የትምህርት ቤት ስለነበር ከርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቦርድ የተላከው አራት ሺ ዶላር ለዚህ እንዲውል ጉባኤ በአንድ ኃሳብ ተስማምቶ የመሰረት ድንጋይ እንዲጣል ተወሰነ፡፡

ሌላው ብዙ ወጪ ሳያስወጣ የገቢ ምንጭ የሚያስገኝ የሀገሬው ሕዝብ የሚወደው ጥል እንደገዛና ቦታው ተፈልጎ በአስቸኳይ ሥራ ላይ እንዲውል ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ከተላከው ሁለት ሺ አምስት መቶ ውስጥ አንድ ሺ አምስት መቶ ለዚህ መሣርያ እንደውል አምስት መቶው ለትምህርት ቤቱ ማሣርያ ውስጥ እንዲ ጨመር ሆኖ ሥራው እስከ ሚጀመር ከተጀመረ በኋላ ገንዘቡ ባንክ ገብቶ ከዚያ እየወጣ እንዲሠራ በቤተ ክርስቲያኑ አለቃና በምክትል ሊቀ መንበሩ በቺፍ ዮሴፍ በሁለቱ ፊርማ የሚንቀሰቀስ አራት ሺ አምስት መቶውን ዶላር ባንክ በቤተ ክርስቲያኑ ስም እንዲያስገቡ ገንዘቡ ተስጥተቸዋል፡፡ወደዚያ ስንጓዝ በደረሰብን እንግልት ጤና በማጣታችን ፕሌን እንዲፍለግልን ጠይቀን በእጃችን ከነበረው ገንዘብ በላይ

ስለተጠየቅን ገዳመ ተክለ ሃይማኖት ከላከው ውስጥ አምስት መቶ ዶላሩን በብድር እንዲሰጠን ጠይቀን ለፐሌን እንዲውል አድርገናል ። ከአባ ሳሙኤልና ከጆርዳን የተላከውንም አንድ ሺ አምስት መቶ ዶላር በአጠቃላይ ሰባት ሺ አምስት መቶ ዶላር ለጉባኤው አስረክበናል በዚያን ጊዜ የአንድ ዶላር ወደ ሀገሩ ሺልንግ ሲለወጥ ሰባ ዘጠኝ እንደነበር ተነግሮናል በየጊዜው ክፍና ዝቅ እደሚልም ተገልጾልናል።

ሌላው የሀገሩን ሠርዶ በሀገሩ በሬ እንደሚባለው» ወደፊት ክርስትናው እንዲጸና እንዲዳብርና እንዲሠፋ ለማድረግ ከትርኪና ብሔረ ሰብ ከዲያቆናቱ ሦስት ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ተወሰወደው የአብነት ት/ቤት ገብተው እንዲሰለጥኑ ቢደረግ ተመልሰው ያን ኅብረተ ሰብ ማገልገል ቢችሉ ሲል ጉባኤው ጠይቋል በመሠረተ ኃሣቡ በአበልቲ ኪዳን ምሕረት ገዳም በኢትዮጵያ ከተለያዩ ብሔረ ሰብ ወጣቶች እንደሚሰለጥኑ ተረድተናል እነዚህን እስፖንሰር የሚያደርጉ በጎ ፈቃድ የአላቸው ምዕመናን ተፈልገው ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስም ይህ ዓለማቸው ስለሆነ አዳሪ ትምህርት ቤት ስለሚያስገቡልንና ልጆቹም ወደዚህ ቢገቡ የባይተዋር መንፈስ ስለማይሰማቸው ይህን ኃሣብ በእኛም ኃሣብ ውስጥ ስለነበረ እስፖንሰር የሚሆናቸው በማፈላለግና ትምህርት ቤቱን በተመለከተ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስን ለማስፈቀድ ተስማምትን እነሱም በዚያ በኩል የአለውን የልጆቹን መምረጥ በመንግሥት በኩል የሚደረገውን ቅድመ ዝግጅት የማስፈጸሙ ኃላፊነት የእነሱ መሆኑ ተነገሮአቸው ተስማምተዋል።

## *አሥራ ሰባተኛ ቀን ሐሙስ የካቲት አሥራ ሁለት ቀን 2001 ዓ.ም*

ዕለቱ ቅዱስ ሚካኤል በመሆኑ ቀደም ብለን ከጧቱ አሥር ሰዓት ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄደ የነገሀ ጸሎት በማድረስ ቀዳሴ በመቀደስ ለማኅበረ ምዕመናኑ ትምህርት በመስጠት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገውን በዚህ ዓይነት ፈጸምን ከሰዓት በኋላ ለሚደረገው የመሠረት ድንጋይ ማኖርና እኛም የመጨረሻ ቀናችን መሆኑ ተገለጸ ሁሉም እንዲገኙ ማሳሰቢያ ከተሰጠ በኋላ ከምዕመናኑ በአንዱ ቤት ምሳ ተጋብዘን ወደ ማረፍያችን ሂደናል።

ከሰዓት በኋላ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ህጻናቱ ጭምር እንዲሁም የቱርካናው ኅብረተ ሰብ ተገኝተዋል የሠርክ ጸሎት አድርሰን

ስለመጣንበት ስለወደፊት የክርስትናቸው ጉዞ ስለአደረጉት የህንፃ ቤተ ክስቲያን ግንባታ ትጋታቸው ምስጋና ወደፊት እንዴት በክርስተና ሕይወታቸው መጓዝ እንደሚገባቸው ገለጻ ተደርጓል፡፡ ከእነሱም አስታያየት ተሰነዘሯል ጥያቄ ተጠይቋል በዚህ ዓይነት በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የሚደረገው መርሐ ግብር እንደተፈጸመ ሁሉም ወደ ውጪ በመውጣት በጭብጨባ በእልልታ እየተዘመረ የት/ቤቱ መሠረት ተጥሎ እንዳበቃ የአስጀመረ አምላክ እንዲያስፈጽመን መዝሙር ዘምርን ጸሎት አድርሰን የመጨረሻ ስንብት አድርገን ወደ ማረፍያ ቤታችን ገብተናል፡፡

## *አሥራ ስምተኛው ቀን ዓርብ የካቲት 13 ቀን 2001*

ዓርብ የቺፉ ወንድም በናይሮቢ የሚኖር ባለሥልጣን ለስደተኞች ኢትዮጵያውያን ድጋፍ የሚሰጥ ቤተ ክርስቲያኑ ህጋዊ አካል እንዲኖረው ጥረት የአደረገ ለመጠመቅ እየተማረ የአለ አቶ ሲልቨስተር ኩያ( )በሥራ ብዛት ቀደም ሲል ባይኖርም ለተወሰነ ጊዜ ከእሱ ጋር ስብሰባ አድርገን ለወደፊቱ እንዴት ተደርጎ አብያተ ክርስቲያናት የሚታነጹበትን ወደ እምነቱ የገቡት እምነታቸው የሚጸናበት ምግባራቸው የሚቀናበትን ወደ እምነቱ የአልመጡት እንዴት ወደ እምነቱ የሚመጡበትን በሠፊው ኃሣብ ለኃሣብ ተለዋውጠናል የአድራሻ ልውውጥ አደርገን በካኩማ የሚደረገውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሥራ የጉብኝት ጊዜ ፈጽመን ናይሮቢ ወደ ሚያደርሰን አየር መንገድ በታክሲ አቀናን የአካባቢው አባት ቀሲስ አለሙ ማሞና ሌሎችም ስደተኞች ወገኖቻችን እስከ አየር ማረፍያው ድረስ በፍቅር አሸኛኘት ሸኝተውን ተመለሰዋል፡፡

## *አስራ ዘጠነኛ ቀን ቅዳሜ የካቲት 14 ቀን 2001 ዓ.ም*

ዓርብ ከካኩማ በፐሌን ተሳፍረን ናይሮቢ ደረስን አበበና ሽመልስ ተቀበሉን በታከሲ የአዘጋጁልን ቦታ አረፍን ቧት ቅዳሜ ከተማውን ተመለከትን ከአንዳድ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ጋር ስለእነሱም ስለቤተ ክርስቲያን ውይይት አደርገን ወደ ኤርፖርት ተጓዝን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አዲስ አበባ ደረስን የአልገመትናቸውና የአልጠበቅናቸው ብፁዕ አባታችን አቡነ ቀውስጦስም በኤርፖት በመገኘት በቡራኬ ተቀብለውናል የብፁዕነታችውን ቡራኬ በማግኘታችን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር እንደነበረ ማረጋገጥ ችለናል፡፡የበርሃው ጉዞ አድካሚ ስለነበር በአረፍንበት አካባቢ ቅዳሴ ከማስቀደስ በቀር የሥራ ጉብኝት ሳናደርግ ሁለቱን ቀናት በእረፍት አሳልፈናል፡፡

## *ሃያ ሁለተኛ ቀን ማክሰኞ የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም*

በዚህ ዕለት በሐዋርያት ሥራ በምዕራፍ 4 በቁጥር 34 የተጻፈውን ዓላማ የአደረገ የሐዋርያትን ሥርዓተ ማኅበር ለመኖር እንቅስቃሴውን ቅድመ አብዮት የተፀነሰ በአብዮቱ ተወልዶ መዳኅ የጀመረ ዛሬ ጎልምሶ ህጋዊ ሰውነት አግኝቶ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን ማኅበረ ምመናን ለመታደግ ስበከተ ወንጌልን በሀገር ውስጥ ሆነ ከሀገር ወጪ ለማዳረስ ቆርጦ የተነሳ በጎ አድራጎቱን በማስፋት ጠዋሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያንና አረጋውያት በመጦር ወላጅ አልባ ህፃናትን የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ እየሰጠ የሚያስተምር በዓለም ውስጥ እያለ በሌላ ዓለም የአለ በከተማ እያለ ገዳማዊ ኑሮ የሚኖር በኢትዮጵያ ሀገራችን የመጀመርያውና ምትክ የሌለው ምሳሌ የማይገኝለት እራሱን ደብቆ የኖረ የሚኖር«ኢትክል ተከብቶ ሀገር እንተ ተሐንፀት መልዕልተ ደብር»እንደሚለው ወንጌሉ የሚሠራው ሥራ ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ በመሄዱ ሳይወድ በግድ እኛ ም በጆሮ የሰማነውን በዓይን አይተን በአካል ተገኝተን ውነቱን ለማወቅ «ጽርሐ ጽዮን ዘተዋኅዶ የአድነት ኑሮ ማኅበር»ወደ ተባለው ድርጅት አመራን፡፡ስለድርጅቱ አመሠራረት ዓለማውና ግቡ በጉዞው ላይ የአጋጠመው በአጠቃላይ የማኅበሩን መዋቅር አንድ በአንድ ሠፊ ማብራርያ በማኅበሩ የየከፍል ኃላፊዎች ከተደረገልን በኋላ በተግባር አንድ በአንድ እየተዘዋወርን ተመልክተናል፡፡ በውነት የንግሥተ ሰባ ታሪክ ትዝ አለኝ ንግሥቲቱ ስለሰሎሞን ጥበብ የሰማቸውን ለማየት ጓጉታ ረዥም ጉዞ ተጉዛ ደርሳ በተመለከተች ጊዜ ከሰማቸው ይልቅ የአየቸው አጅግ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ እንደ ሰማይና ምድር የተራራቀ ሆኖ እንዳገኘ ችው ሁሉ እኛም እንደዚያ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በማለቅ ላይ የአለው የስብከተ ወንጌል ማሰልጠኛው መማርያ የተማሪዎቹ ማደርያና የመጻሕፍት ቤቱ ከፍሎችን የያዘው ህንጻ እስከ ሰምንተኛ ከፍል አራት መቶ በላይ ህፃናት ቀን ከሦስት መቶ በላይ የማታ ትምህርት የሚሰጥባቸውን የመምህራኑን ጥራት የግቢውን ጽዳት የዛፎች የአበቦችና የጓሮ አትክልቶች በሥነ ሥርዓት መያዝ፡ የበጎ አድራገጎቱን ክፍል አረጋውያንና አረጋውያት የሚጦሩበትን ህፃናት የሚያድጉበትና የሚረዱበትን የበጎ አድራጎት ከፍል የፋይል አየያዝ  ለቤተ ክርስቲያን ሕይወታቸውን የሰጡ ቀደም ሲል እነ ላቀው አዴሳ ሲረዱ እንደነበርና በዚያው እንደተቀበሩ ዛሬ በሕይወት የአሉ እነ ሊቀ ጉባዔ አበራ በቀለ እንደሚጦሩና በጥሩ ሁኔታ እንደተያዙ ተመልክተናል፡፡

የምግባረ ልማት ከፍሉ የኦቾሎኒ ማምረቻውን ከመጀመርያው ሥራው ጀምሮ እስከ ፍጻሜ የሚካሄደውን የሰራተኞች አሠራር ጥንካሬ በጎ ፈቃድና ትህትና ስናይ የዓለመ መላእክትን አሠራር ያስታውሳል።የተግባር ቤቱ የእንጀራ መጋገርያው ወጥቤቱና ጠላ ቤቱን እንዲሁም የመመገቢያቸውን አዳራሽ ተመልከተናል የአለው አርባ አባ ወራ ከአባ ወራው የሚበልጠው ቤተ ሰብ በሙሉ የሚመገበው አንድ ዓይነት በተወሰነ ጊዜ ሁሉም በአንድነት በገዳሙ የሌለ በዚህ ሲፈጸም በማታችን እግዚአብሔርን አመስገነናል የምግብ አድነት ብቻ ሳይሆን የጥሪትም አንድነት አላቸው ለምሳሌ በሺ የሚቆጠር ደመውዝ የአለው በመቶ በሃምሳ ከሚቆጠር ደመወዝ የተለ አይደለም ሁሉም በአንድ ቋት ይሰበሰባል በዘመናችን በሀገራችን የመጀመርያው የሐዋርያትን ሥርዓተ ማኅበር የሚፈጸምበትን በማየታችን መደነቅ ብቻ ሳየሆን እግዚአብሔር አምላክ በሥጋ ዓይን ሲታይ ይህንን የማይቻል  አንድነት ኑሮ መቻሉን ስለሰጣቸውና  በዚህ ዘመን የሐዋርያትን ሥርዓተ ማኅበር በተግባር የሚታይ ሥራ እየተሠራ በመሆኑ የተዋኅዶ እምነት ተከይ የሆነ ሁሉ ያን ቦታ ቢያይ አስፈላጊውን እርዳታ ቢያደርግ እያንዳዱ ምዕመን ወይንም ሃይማኖታዊ ድርጅት ሊሠራለት የሚፈልገውን ሁሉ እሱ እንደሠራው ተሠርቶ ያገኘዋል የሚል እምነት አለኝ በዚህ ዓላውያን መናፍቃን ቤተ ክርስቲያናችንን ከመውረር አለፈው ምዕናን ከህናትን እያረዱ አብያተ ክርስቲያናትን እያቃጠሉ እንደሆነ ፀሐይ የሞቀው ዓለም የአወቀው እንደሆነ ግልጽ ነው።እኔ በዚህ የበጎ ፈቃድ የአገልግሎት ጉብኝቴ በዞርኩባቸው ሁሉ«አብያተ ክርስቲያናት ይታፀዋ አብያተ ጣኦታት ይትረሐዋ» ተብሎ የታወጀበት ዘመንን  ይመስላል በግራ በቀኝ የጨረቃ ምስል የተቀረፀበትና  የማስመሰል መስቀል የአላቸው ህፃዎች ነበሩ የሚታዩት የተዋዶ ህንፃ አብያተ ክርስቲያናት አልፈው አልፈው ቢኖሩም አገልጋዮች በፍራትም ሆነ በችግር ምክንያት እየለቀቁ በመሄዳቸው ብዙዎቹ የተዘጉ ናቸው በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ የአሉ በጣት ከሚቆጠሩ በቀር ብዙኀኑ ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ በማለት ከተማውን አንቀው ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው« እሰመ ኅሠተ ረሰይዋ ለጽድቀ እግዚአብሔር» እንዳለው ሐዋርያው በዚህ ግብር የሚኖሩ ናቸው እግዚአብሔር ለመንጋው ስለሚጠነቀቅ በዘመነ ብሉይ ነቢያትን በዘመነ ሐዲስ ሐዋርያት አርደዕትን በዘመነ ሊቃውንት ሰማዕታትን እያስነሳ መንጋው እንዳይበተን እንዳደረገ ሁሉ ዛሬም በሀገራችን እነዚህን የጽርሐ ጽዮንን አባላት ሰባክያንንና መዘምራንን አስነስቶ ለመንጋው መልእክተኛ አድርጎ በመልአኩ ምዕመናኑ በእነሱ እየተጽናና የአለ መሆኑን ለመረዳት

ችያለሁ ። በተለይ በአዲስ አበባ በጽርሐ ጽዮን ማኅበርና በጅማ አበልቲ ኪዳን ምሕረት ገዳም የሚደረገው በየብሔረ ሰቡ በየቋንቋው እያመጡ እንዲሰለጥኑ ማደረጉ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን ትንሣኤን ለማምጣት ከዚህ የተሻለ አማራጭ የሌለ መሆኑን ተረድቻለሁ። ይህ የጽርሐ ጽዮን ዘተዋኅዶ ጅርጅት በግልም ሆነ በማኅበር ሊረዳ የሚገባው ነው። እስከ አሁን የተሰጠውን እርዳታ በተባለው አገልግሎት ላይ አውሎ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆኑን እስከ ዛሬ የሠራው  ሥራ እጅ አውጥቶ የሚጨብጥ እግር አውጥቶ የሚንቀሳቀስ ሆኖ ሥራው ምሥክርነትን ሲሰጥ ይታያል። እኛም በገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር« ከወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ» የተፈቀደውን አምስት ሺ ዶላር ይዘን እንደ መጣንና ገንዘቡም አዲስ አበባ በአለው ንዑስ ኮሚቴ አማካይነት ባንክ እንደገባ ለምን እንደሚያውሉት ከአወቁ በኋላ ከዚያ መውስድ እንደሚችሉ ገልጸን ከኮሚቴው የተላከውን ደብዳቤ ሰጥተን የዚህን ዕለት መርሐ ግብር ፈጽመናል።

## *ሃያ ሦስተኛ ቀን ረቡዕ የካቲት አሥራ ስምንት 2001 ዓ.ም*

በዚህ ዕለት ከአቶ ፍሬው ቡልቡላ ጋር በመሆን ለቤተ ክርስቲያናችን ንዋየ ቅድሳት የሚሠራበትና የሚጋዛበት በመሄድ መጎናጸፊያ የሚሠራባቸውን ሁለት ሦስት ቦታዎች ተመልክተናል የአቶ አድማሱ ሥራው ጥራት የአለው ሲሆን ዋጋው ግን በጣም ውድ ሆኖ አግኝተነዋል።ቀደም ሰል ከመጋቤ ሀብታት ጋር ውልም ተዋወለው ስለነበር ዋጋውን ቀነስ አድረጎ እንዲሠራ ተሞክሯል ሌላው የሥጋው ወደሙ ማክበርያ የሚሆን ከቤተ ክህነቱ ሁለት ገዝተናል የመጻሕፍት መሸጣም ጎራ በማለት መጻሕፍት ገዝተናል ገቢ ገብርኤል ሌላ ሙካሽ የሚሠራ ንቡረ እድ ገብረ ሕይወት አለ ብለውን ሄደናል ሥራው ጥራት የአለው ሆኖ አላገኘነውም በዚህ ሀገር አንድ ጉዳይ ለማስፈጸም አንድ ጀበር አይበቃውም ሥራዎችን በአግባቡና በጊዜ ከመሥራት ይልቅ በማጭበርበር ገንዘብ ለማግኘት መሸዋወድ ይበዛበታል ። ከሰዓት በኋላ ሰለቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ከአንዳድ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ጋር ውይይት በማደርግ ዕለቱ ተፈጸሚል።

## ሃያ አራተኛ ቀን ሐሙስ የካቲት አሥራ ዘጠኝ ቀን 2001

የደብረ ሊባኖስና የፍቼ ጉዞ ቀደም ሲል ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ በጫጋል የድሆች መንደር አገልግሎት ላይ እንዲውል ሃያ አንድ ሺ ዶላር ርዳታ አድርጎ ስለነበር እንዲሁም በአለፉት ሁለት ዓመታት ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ከርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ለሰማዕቱ ቅዱስ ጴጥሮስ ገዳም ህንጻ ቤተ ክርስቲያን መደጎሚያ አሥር ሺ ዶላር በሁለተኛው ዙር ደግሞ ከገዳሙ ኩታ ገጠም ለህጻናት ት/ቤትና አረጋውያን የሚጦሩበትን ህንጻ የሚሠራበት ቦታ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ጠይቀው አራት ሺ ዶላር እንዲሁም ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ ለመቶ ሃያ ህጻናት የትምህርት የደንብ ልብስ መግዣ የሚሆን ጠይቀው ሁለት ሺ አምስት መቶ ዶላር የተሰጠውን ሥራ ላይ መዋሉን ለማየትና በዚያው ገዳሙ ደርሶ ቡራኬ ተቀብሎ በግል ከምዕመናን የተላከውን ገንዘብ ችግር ለጸናባቸው ግለሰቦች ለማድረስ ነበር፡፡እግር መንገዳችንን እራስ ካሣ የአሠሩትንና የተቀበሩበትን እንዲሁም ሌሎችም የራስ ካሣ ቤተ ሰቦችም መቃብር የሆነውን የጫጋል መድኃኒ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና ገድመውት የነበረውንም የድኩማን መርጃም ጎብኝተናል፡፡ በመጀመርያ ጫጋል መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ደረስን በጉዞው የነበሩት ቀሲስ ታዬ ብርሃን ዲያቆን ዘለዓለም ወንድሙ አቶ ፍሬው ቡልቡላ አቶ ጌራ ሚካኤልና ወ/ሮ ራኄል መኩርያ ነበርን እራስ ካሣ የተቀበሩበትን የካህናቱን ኑሮ የተጀመረወን መነኮስያይት የሚሠሩትን ተመለከትናል፡፡ከህናቱ በወር የሚያገኙት ከሠላሳ ብር እስከ አርባ ብር እንደሆነ ቤተ ሰብ እንዳላቸው በቂ ነገር ከአለማግኘታቸው የተነሳ ብዙዎቹ እየለቀቁ ሙሉ አገልግሎት መሰጠት እንዳልተቻለ የመነኮስያይቱም የእጅ ሥራ ደንሚ በአለማግኘቱ እንቅስቃሴው የህን ያህል እንዳልሆነ ተገንዘበናል እነሱም አስረድተውናል፡፡በውጩ የአሉት የራስ ካሣ ቤተ ሰብ በትክክል ቢረዳ ከዚም ተርፎ በአካበባቢው የተዘጉ አብያተ ክርስቲያናትን ማስገልገል ይቻላልና የራስ ካሣ ቤተሰብ የአባቶቻቸውን ሥፍራ እንዲጎበኙ እንዲረዱ በዚህ አጋጣሚ እናሳስባለን፡፡

ሁለተኛው የድሆች መንደር ወደ ሆነው አመራን አረጋውያን ይጦሩበታል ህጻናት ይማሩበታል፡፡አካባቢው በደንብ የተያዘ ይመስላል ለድርጅቱም ገቢ የሚያመጣ የእንግዳ መቀበያ ቦታም ተዘጋጅቷል ድርጅቱ ከገዳሙ ጋር ግንኙነቱን የአወሐደ አይደለም ከቤተ ከህነቱም ጋር ቢሆን እስሰር የለውም እኛም ወደዚያ የተጓዝነው አንደኛው ከገዳሙ ጋር ተውጎዶ

አብሮ እንዲሠራ ሁለቱን ክፍል ለማነጋገር ነበር  የህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ተገኝተዋል፡፡በዕለቱ የድርጅቱን መሥራች ባህታዊ ከፋለውን ማነጋገር ነበር ባህታዊው ከገዳሙ ጋር አብረው ለመሥረትና ድርጅቱንም ለገዳሙ ውርስ ለመስጠት የውል ሰነድ እንደሰጡ ገልጸውልናል ገዳሙ እንቢአለኝ እንጂ ከገዳሙ መለየት አልፈለግሁም አሁንም ቢሆን የተለወጠ ኃሣብ የለኝም ብለዋል፡፡እንዲሁም የወተት ላሞች እንዲኖሩ ጥናት ተጠንቶ በጎ አድራጊዎች የለገሏቸው ላሞች ተሸጥዋል የተገነባውም ቤት በከንቱ ቀርቷል ለምን ሆነ የሚል ጥያቄም ተነስቶ መኖ በመጠፋቱና መሞት ስለጀመሩ ጨርሰው ከማለቃቸው በፊት ለማተረፍ ተሸጠዋል  ገንዘቡም አለ ሲሉ ገልጸዋል በዚሁ ዙርያ በርካታ ውይይቶች ከተደረጉ በኋላ ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት መሠረቱ ገዳሙ እንደመሆኑ መጠን ደካሞቹም ከገዳሙ የመጡ በመሆናችው መሥራቹም ባሕታዊ ከፋለውም የገዳሙ ዓባል በአለመቁነን እንደመሆናቸው መጠን ከገደሙ ጋራ የውስጥ መመርያ ወጥቶለት አብሮ እንዲሠራ ገዳሙ ፈቃደኛ ከአልሆነ ከቤተ ክርስቲያን መውጣት ስለሌለበት በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የበላይ አመራር የውስጥ መመርያ ወጥቶለት ምዕመናንንም ከህናትንም የአቀፈ ከልዩልዩ ክፈሎች የተወጣጣ ቦርድ(ኮሚቴ) እንዲ ቋቋም ገዳሙን ለማነጋገር ብፁዕነታቸው ገዳሙን እንዲያነጋግሩ ለሰኞ የካቲት ሃያ ሦስት ቀን ቀጠሮ በዚህ ዙርያ የሚያደርገውን ውይይት ፈጽሟል፡፡

ከወገን ነፍሰ አድን ኮሚቴ ስለተላከው ሃያ አንድ ሺ ዶላር ምን እንደ ደረሰ ምን ላይ እንደዋለ ገንዘቡ እንደ ደረሰዎትና አንዳድ ሥራዎች ላይ እንደዋለ ሪፖርት ተደርጎልናል ያ በደብዳቤ የተገለጸውን በተግባር ማየት እንፈልጋለን፡፡ብለን ለጠየቅናቸው እኔ ገንዘባችሁን በማይንቀሳቀስ ሁልጊዜ ምርት መስጠት የሚችል ላይ ነው የአዋልኩት በማለት ከአንድ ጋሻ መሬት የአለነሰ ቦታ እንደተገዛበት የከብት እርባታ የሚካሄድበት ትልቅ አዳራሽ እንደተሠራበት  አዙረው አሳይተውናል አቅም በማጣትና ከገዳሙ ጋር መግባባት በአለመኖሩና ከእናንተም ድጋፍ በማጣታችን የባሕር ዛፍ ከመትከል በቀር እንደታሰበው ሥራው ሊንቀሳቀስ አልቻለም አሁንም ከፈለጋችሁ የእናንተ ደርጅት ኃላፊነቱን ወስዶ የፈለገውን ሊሠራበት ይችላል ሲሉ ገልጸውልናል፡፡

ሦስተኛ ፍቼ የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስን ገዳም ሁኔታ ለማየት ከብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ ጋር አምርተናል፡፡እንደ ደረስንም ብፁዕ አባታችን ስለህንፃ ቤተ ክርስቲያኑና ስለጠቅላላው የገዳሙ ይዞታ አስረድተውናል፡፡በመቀጠልም ከርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት

ማርያም ቤተ ክርስቲያንና ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት ስለተሰጠውም ገንዘብ አንስተው በመጀመርያ የወሰድኩት አሥር ሺህ ቦታውን እያስጎበኙ የምታዩትን አብነት መምህራን መኖርያና ለህንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ድጋፍ እንደሆነ ያ የእናንተ ድጋፍ ባይኖር ህንፃ ቤተ ክርስቲያኑ አሁን በአላበት ፍጻሜ ላይ በአልደረሰም ነበር በውነት የዋሽንግተን ዲሲ ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የአደረገቸውን አስተዋጽኦ በማድነቅ ቤተ ክርስቲያኒቷ ብቻ ሳትሆን የቤተ ክርስተያናችሁ አባላት የሆኑ እነ አንተነህን የመሳሰሉ የመሰኮቶችን መስታዎቶቹንና መንበሮቹን የሸፈኑ መሆናቸውን ገልጸውልናል፡፡ በሁለተኛው የተሰጠኝ አራት ሺ ዶላር እናንተንም የጠየቅሁት ኩታ ገጠም የሆነውን ቦታ አግንቼ ገንዘብ በማጣት የተነሳ ሌላ ግለሰብም ሆነ ድርጅት እንዳይወስደው እርዳታ እንዲደረግልኝ ስለነበር ይህ ሰፊ ቦታ ተገዝቶበታል  ይህም ቦታ የሚውለው ለትምህርት ቤት ስለሆነ እንደምታዩት ግንባታውም ተጀምሯል፡፡ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን የተሰጠኝ ሁለት ሺ አምስት መቶ ዶላር ስትገቡ እየዘመሩ የተቀበሏችሁ ለመቶ ሃያ ተማሪዎች የደንብ የትምህርት ቤት ልብስ ተገዝቶላቸው ለብሰው የአያችሁት ነው፡፡ሲሉ ሰፊ ማብራርያ ሰጥተውናል፡፡በውነቱ እንዳየነው እንደተመለከትነው በዚያ ቦታ የሚደረገው እንቀስቃሴ በጣም የሚያስደሰትና ውጤታማ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ተገነዝበናል ድጋፍ ቢያገኙ የበለጠ ይሠራሉ ብለን እንገምታለን፡፡

## ሃያ አምስተኛ ቀን ዓርብ የካቲት ሃያ 2001 ዓ.ም

በዚህ ቀን ሁለተኛው  ወደ ወላይታ ጉዞ ጉዞው በሕዝብ አውቶቢስ ስለነበር አድካሚና አሰልች ነበር የአንድ ቀን አዳር አድርጌ ተመልሻለሁ ፡፡ በመጀመርያው ጉዞየ የአለጠናቀቅሁት የግሌ ጉዳይ ስለነበር ያን ለማጠናቀቅ ነበር ሌላው ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ በመጀመርያው የወላይታ ጉዞ ተገዝግቧል፡፡

## ሃያ ስድስተኛ ቀን ቀዳሜ የካቲት 21 ቀን 2001 ዓ.ም

ይህ ዕለት ሁለተኛው ከወላይታ ጉዞ መልስ የአደረኩበትና ምሽቱን ወደ ጽርሐ ጽዮን በመሄድ የአሰለፍኩበት ከጠቅላላው የማኅበሩ አባለትና ቤተ ሰብ ጋር በመገናኘት የስርክ ጸሎት በማድረስ  ስለቤተ ክርስቲያናችንና ስለእምነታችን የጋራ ውይይት በማደረግ በዚያው አድሬአለሁ፡፡በማግስቱም እሁድ የካቲት 22 ቀን 2001 በገዳሙ ውስጥ

ወደ አለው የአባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትና የእመቤታችን የልደቷ መታሰቢያ የሆነ ታቦታተ ህገጋቱ ወደ አሉበት ቤተ ክርስቲያን በመሔድ ከጠቅላላው የማኅበሩ ቤተሰብ ጋር የነግህ ጸሎት አድርሰናል፡፡በሠርኩና በነግሁ ጸሎት የአየሁት የአስደሰተኝ ነገር ቢኖር የህፃናቱ ትጋትና ለጸሎት የሚያድርጉት እሽቅድድም ንባቡን ሲያነቡት ዜማውን ሲያዜሙ ከብሔረ መላዕክት የመጡ ይመስላሉ በዚህም እግዚአብሔርን አመስግኛ ለሁ፡፡ከዚያም ጋሽ አበራ በቀለን ጎብኝቻለሁ ጋሽ አበራ ማለት በፊት ጥቁር እራስ በነበሩበት ጊዜ የምንጠራበት የአቅርቦት ቅጽል ነበር በኋላ መንኩሰው ሊቀ ጉባኤ የሚል ስያሜ አግኝተው የሰበካ ጉባዔ መምርያ በመሆን ሲያገለግሉ የኖሩ ናቸው ታማሚ ሆነው በጽርሐ ጽዮን ግቢ ውስጥ ቤት ተሰርቶላቸው በዚያ እየተረዱ ይኖራሉ፡፡ ሊቀ ጉባዔ አበራ ማናቸው የሚል ቢኖር  ውጫው ዓለም ድረስ በመሄድ ተምረው የዩነቨርስቲ መምህር በመሆን በዘመኑ ትልቅ ደመወዝ የሚከፈላቸው የነበሩ የእግዚአብሔር ምሪት ያን ብዙና ትልቅ ደመወዛቸውን በመቀነስ በአነስተኛ ደመውዝ ወደ ቤተ ክህነት በመግባት ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት አግኝታ እንድትቀሳቀስ የአበቁ ታላቅ መሰዋትነትን የከፈሉ ቃለ አውዲውን በተግባር ሥራ ላይ እንዲውል የአደረጉ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን በአለውለታ ናቸው፡፡

## ሃያ ሰባተኛ ቀን ሰኞ የካቲት 23 2001 ዓ.ም

ሁለተኛው የደብረ ሊባኖስ ጉዞ የነበሩ ሊቀ ትጉሐን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኜ አቶ ፍሬው ቡልቡላ አቶ ጌራ ሚካኤል ብርሃኑ ነበሩ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስም ከፍቼ መጥተዋል በቀጠሮው መሠረት ከብፁዕነታቸው ጋር በመሆን ወደ ቤተ ምርፋቁ ገባን ፀባቴውም ተገኝተዋል ብፁዕነታቸው ሰበሰባው በጸሎት ከፍተው የሰበሰባውን ዓላማ ገለጻ አድርገዋል እኔንም ኃሳብ እንድሰጥ ጠይቀውኛል፡፡እኔም« እድሉ እንዲሰጠኝ በመደረጉ በማመስገን በመሠረቱ ስለዚህ ጉዳይ ድርጅቱና ገዳሙ አብረው እንዲሠሩ በ2004 መጥቼ በሠፊው ተነጋግረናል ፓትርያሪኩም ገዳሙንና ድርጅቱ አብረው የሚሠሩበት መመርያ ስለሚያስፈለገው አዘጋጅተው እንዲያቀርቡ ለህገ በለሞያ ተእዛዝ እንደተሰጠና እስከ አሁን ምንም ነገር እንደሌለ ባህታዊም ብቻቸውን እየሠሩ ስለሆነ በዚህ ዓይነት አሠራር እኛም ድጋፍ መስጠት ስለማንችል ድርጅቱንና ገዳሙ በኅብረት የሚሰሩበትን የውስጥ መመርያ ቢዘጋጅ የገዳሙ ተወካዮች የሚሳተፉበት ፀባቴው የሚመሩት ቢሆንና ባሕታዊ እንደመሥረች ቋሚ የቡርዱ(የኮሚቴው) አባል ሆነው

አስተዳደሩን እንዲመሩ ቢደረግና በአዲስ መልክ ቢዋቀር ለገዳሙም ለተረጂዎችም እርዳታውን ለሚሰጡትም ሁሉ የዚህ አሠራር ጠቃሚ ይመስለኛል» ስል የገለጥኩትን ሊቀ ትጉሃን ኃ/ጊዮርጊስ ዳኜ ይህንኑ በመደገፍ ከዚህ ቀደም የሰላሌ ሀገረ ስብከት ሥራ አስካጅ በነበርኩ ጊዜ ከገዳሙ እዳይለይ ስምምነት ተደርሶ እነደነበረና እኔ ተቀይሬ ወደ ሌላ ስሄድ ነገሩ ሳይታሰር እንደቆየ ገልጸው አሁንም በተባለው መሠረት ከገዳሙ በአልተለየ ሁኔታ የኅብረት ሥራውን ለመሥራት ቢጀምር መልካም ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ጸባቴው አባ መሐሪ የቀረበውን ኃሣብ ወድቅ በማደረግ ባሕታዊው እየለመኑ የሚያደረጉትን እርዳታ አንቃወምም እኛ ግን እዚያ ሂደን ለመርዳት አንችልም እዚህ የአለውንም ማሟላት አልቻልንም ስምንት መቶ በአለ መቁነን አስር ሺ የሚሆነው ደግሞ በገዳሙ ሥር ተጠልሎ የሚኖር ይህ ሁሉ በገዳሙ እርዳታ በልቶ የሚያደር ነው ይህ ሁሉ የእኛ ኃለፊነት ነው ሌላ ኃለፊነት መጨመር ይከብደናል ከዚህም በአሻገር ቅዱስነታቸው የገዳሙ ኃላፊ እንደ መሆናቸው መጠን ይህን በተመለከተ መመርያ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ለህግ ከፍል እንደተላለፈና በህታዊ መመርያው እስከሚዘጋጅ እስከ አሁን እንደሚያደርጉት ሥራውን ይሥሩ የሚል ደብዳቤ እንደደረሳቸው በወሬ ደረጃ ሰምቻለሁ ያ ለእሳቸው ተጻፈላቸው የተባለው እኛ በግልባጭ ልናውቀው በተገባ ነበር ያም ሆነ ይህ ከቅዱስነታቸው መመርያ ውጪ ምናደርገው አይኖርም እኛ እስከ አሁንም ከባህታዊ ጋር ችግር የለብንም የአገኙት የነበረውን አበል (መቁነን) አልተከለከሉም አንዳድ የሚያስፈልገን ነገር ሲኖር ይታዘዛሉ አስፈላጊውን ነገር ያስፈጽማሉ ይፈጽማሉ ከእሳቸው ጋር በዚህ ዓይነት ስመምነት ነው የአለነው ሌላው ኑዛዜ ስለሚሉት ሰነዱን አሰፈጽመው ማምጣት የአለባቸው ባህታዊ ናቸው እንጂ እኛ አይደለንም ቢሆንም አስፈላጊ ከሆነ ባህታዊው ይንገሩኝ በዚህ ዙርያ ያስፈልጋል የሚሉት ከአለ ለመተባበር ወደ ኋላ አልልም ሲሉ ማኅበሩ ከዚህ ወጪ ኃሣብ ከአለው ማቅረብ ይቻላል በማለት እሩሩን ወደ ማኅበሩ ጣሉት ከእሳቸው ኃሳብ የአልተራራቀ ከአባቶች ኃሣብ ቀረበ ነገሩ የተዘጋ በመሆኑ ብዙ መነጋገር ሳያስፈልግ ጉዳዩ ቅዱስነታቸው ጋ ስለሆነ ብፁዕነታቸውም ሆኑ ገዳሙ እንዲሁም ባህታዊ ተከታትለው አንድ ፍር ላይ ማድረስ ወይም ሀገረ ሰብከቱ ኃለፊነቱን ወስዶ መዋቅር በአለው አሰራር እንዲሠራ እንዲደረግ የመጨረሻ ኃሣብ ላይ በመደረስ የዕለቱ ሰብሰባ በጸሎት ተፈጽሟል።ይህ የተባለው ድርጅት ህጋዊ አካል አለው ህጋዊነቱንም የአገኘው ከፍትሕ ሚኒስተር ነው ባህታዊው እንደሚሉት

*ለመሥራት ምንም የሚከለክላቸው እንደሌለ ከክልሉም ጋር አብረው መሥራት እንደሚችሉና እኔ ገዳማዊ በመሆኔ ነው ከገዳሙ እንዳይለይ ጥረት የማደርገው በማለት ደጋግመው ሲናገሩ ይሰማሉ እኛ አረግጠኞች የሚያደርገን በተግባር ሆኖ ስናየው ነው እንጂ የቃሉንማ ልብ የአሰበውን ኩላሊት የአመላለሰውን መርምሮ የሚያውቅ ለእሱ ለባለቤቱ ከመተው በቀር የምንለውም የለንም የምንለው ነገር ቢኖር አረጋውያንና አረጋውያት እንዲሁም ወላጅ አልባ ህጻናት ሊረዱ ይገባል እንላለን፡፡ባህታዊው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ እናደንቃለን በትጋታቸውም እግዚአብሔርን እናመሰጋለን፡፡ አሜን*

## <u>*ሊተገበር የሚገባው ማሳሰቢያ*</u>

*ይህንን የበጎ ፈቃድ የአገልግሎት የሥራ ጉዞ ዘገባ(ሪፖርት) ለምትመለከቱ አባቶቼ እናቶቼ ወንድሞቼና እህቶቼ እንዲሁም የመንፈስ ልጆቼ የሆናችሁ ሀገሬን አወዳለሁ ሕዝቤን አከበራለሁ እምነቴን አፀናለሁ ቤተ ክርስቲያኔን እታደጋለሁ ለምትሉ ወገኖቼ ሁሉ አቀበቱን ወጥቼ ቁለቁለቱን ወረጄ እናንተን መስየ « ከመ ዘነአምር ንነገር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንከውን» የማውቀውን የሰማሁትንና የአየሁትን ስገልጽላችሁ ምን እናድርግ የሚለውን ጥያቄ ማቅረባችሁ ስለማየቀር« ከመዝ ግበሩ» እንዲህ ቢደረግ ሁላችንንም ከእግዚአብሔር ፍርድ ከታሪክ ወቀሳ ነፃ ያደርገናል ብዬ የማምንበትን ከአየሁት ከሰማሁት ከተሰጠኝ መረጃ በመነሳት እንደሚከተለው ሳቀርብ በታላቅ ትህትናና አክብሮት እንደሚከተለው እከትባለሁ፡፡*

*1. ዛሬ ሀገራችን በሚልዮን የሚቆጠሩ ችግረኞችና ረሀብተኞች የሚኖሩባት የምጣኔ ሀብት የማኅበራዊ ሕይወትና የፖሊቲካ ውስብሰብ ችግሮች  የአሉባት መሆኑ ሀገር የአወቀው ፀሐይ የሞቀው የአደባባይ ምሥጢር ስለሆነና የዓለምን ማኅበረ ሰብ ትኩረት ስለሳባ በመንግሥት ጥያቄ መሠረት ዘላቂ መፍትሔ የሚያመጣ ባይሆንም ጊዜያዊ እርዳታ እየገባ ነው፡፡  በገዳማትና በየአብያተ ክርስቲያናቱ ይህ ዓይነቱ እድል ጎልቶ አይታይም በገረገረዋ ተጠግተው የሚኖሩ የሃይማኖት ወገኖቻችን ካህናትና ምዕመናን ችግረኞች ቁጥር ብዛት ከልክ የአለፈ በመሆኑና መጽሐፋችንም« ወፈድፋደሰ ለሰብኣ ሃይማኖት» ስለሚለን ቋሚና ዘላቂ በሆነ መንገድ ገዳማትንና አብያተ በክርስቲያናትን በግል ሆነ በማኅበር ወጥ በሆነ መንገድ በድርጅታዊ አሠራር በሚያቀርቡት ፕሮፖዘል*

መሠረት ቅደም ተከተል በማስያዝ የአለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት በማጠናከር እርዳታ ቢደረግ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት የአለው ችግር ከሦስት ዓመታት እስከ አምስት ዓመታት እንደሚቃለል ከአምስት ዓመታት እስከ አሥር ዓመታት ደግሞ እንደሌሎች አሃት አብያተ ክርስቲያናት ከተረጅነት ወጥተው እርዳታ ሰጭዎች እንደሚሆኑ እገምታለሁ፡፡ለምሳሌ

ሀ. በጅማ ሀገረ ስብከት. መረዋ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ዙርያ ተንጣሎ የአለው ሠፊ ኩዳድ በዘመናዊ መልክ ቢሠራበት ከዚያ የሚመርተው ከቤተ ክርስቲያን አልፎ ለአካባቢው እንደ ሚተርፍ ይገመታል በአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሰን ቅድስት ኪዳነ ምሕረትና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአድነት ገዳምና የደብረ ምሕረት ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ሠፊ የጥምቀት ቦታ ላይ በአቀዱት እቅድ በቀረፁት ፕሮፖዛል መሠረት ተግባራዊ ማደረግ ቢቻል ለቤተ ክርስቲያናችን በሞዴልነቱ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ብዬ አምናለሁ ፡፡ ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ የመሥራቱም የማሠራቱም የመፈጸሙም የማስፈጸሙም ችሎታውም ፈቃዱም እምነቱም አላቸውና፡፡

ለ. በጋምቤላ ክልል ሀገረ ስብከት ከሁለት ጋሻ መሬት በላይ የአለው መካነ ቅዱሳን ዳግማዊ አስቄጥስ ገዳምና በጎደሬ ወረዳ በሐይቅ የተከበበ ገዳመ ቆሮቶስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ክርስቶስ ሠምራ ገዳም ሰፊ ቦታና ለልማት የሚስማማው ሁለቱ ቦታዎች ብቻ ቢለሙ በጋምቤላ ክልል ለአሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ማስትዳድር እንደሚችልና ለሌላም ሀገረ ስብከት እንደሚተረፍ እርግጠኛ ነኝ በትክክል መሥራቱና ማሠራቱ ከተቻለ፡፡

ሐ. በከፋ ሀገረ ስብከት የአቡነ ሐራ ድንግል ገዳምና ሚዛን ተፈሪ የሴቶች መነኮሳይያት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ለሴቶች መነኮሳይያት የገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን በሃምሳ ሺ የኢትጵያ ብር የገዛላቸው የተጣለለ ሠፊ የአትክልት ቦታ እንዲሁም መንግሥት ለትምሕርት ቤት መሥርያ የሰጣቸውን ሥፍራ የሚያለሙበትንና የሚሠሩበትን ድጎማ ማስፈለጉንና የአቀረቡት የሥራ እቅድ ድጋፍ አግኝቶ ቢተገበር ውጤታማ እንደሚሆኑ አምናለሁ፡፡

መ. በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ታላቁ የአባታችን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የደብረ ሊባኖስ ገዳም በገዳሙ ላይ ችግር ይፈጥሩ የነበር የውሻ ገደል ነዋሪ ለገዳሙ እንዲለቁ መንግሥት ለገዳሙ በመወሰኑ ለነዋሪው ህዝብ ግምት ስጥቶ ቦታውን ለልማት ማዋል፡፡በጫጋል የተቋቋመው ብዙ አረጋውያንና አጋውያት የሚጦሩበት ወላጅ አልባ ህፃናት የሚያድጉበትና የሚማሩበት የድሆች መንደር ቀደም ሲል የገዳመ ተክለ ሃይማኖት የወገን ነፍስ አድን ለዚህ ድርጅት በሰጠው ሃያ አንድ ሺህ ዶላር ሠፊ ቦታ ስለተገዛበትና ቦታውም ሳይለማ ሥራ ፈትቶ ስለአለ ያን በማልማት በእርዳታ ከሚንቀሳቀስ አምራች ሆኖ እራሱን በራሱ እንዲረዳ መደገፍ እንዲሁም በዚያው በጫጋል መድኃኔ ዓለም የራስ ካሣ መቃብር የአለበት መነኮሳይያቱ የሚሠሩትን የጎጀ እንዱስትሪ የእደ ጥበብ ሙያ የበለጠ ማምረት እንዲቺሉ መደገፍ በፍቼ ከተማ የሰማዕቱ የአቡነ ጴጥሮስ ገዳም በአለበት በርካታ ህፃናት የሚማሩበትና የሚረዱበት በርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅደስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ እርዳታ በተገዛው ቦታ ላይ ለገዳሙ በቋሚነት የሚረዳበት የልማት ሥራዎች እንዲኖር ማድረግ

ሠ. በደቡብ ክልል በወላይታ ዞን ጻድቁ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በሕየወት እያሉ ከደብረ ሊባኖስ ገዳም በፊት ታላላቅ ገቢረ ተአምራት ወመንክራት የአደረጉበት ለወላይታ ሕዝብ ትልቅ የክርስትና ሕይወት የአስጨበጡበት እንዲሁም ሦስተኛው ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የብሕትውናና የስብከተ ወንጌል አገልግሎት ይሰጡበት የነበርው ደብረ መንክራት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምና የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን ሠፋፊ ቦታዎች ስለአሏቸው በልማት መልክ ማደራጀትና ማቋቋም የመሳሰሉትን ማደረግ፡፡

እነዚህን በቦታው ተገኝቼ በማየቴ ለናሙና ያህል ቀረቡ እንጂ በመላዋ ኢትዮጵያ ግዛቶች በአሉ ሀገረ ስብከቶች ሁሉ የአለ ስለሆነ በውጪ የአለችው ቤተ ክርስቲያን እርዳታንና ልማትን በተመለከተ የጳውሎስ የጵሎስ የኬፋ መባባሉን አስወግዳ አንድ በመሆን «አነ ዘክርስቶስ» በማለት የነበረውን የበጎ አድራጎት ተቋም በማጠናከርና የልማት ኮሚቴ በማቋቋም በቅደም ተከተል ሥራው እንዲሠራ ቢደረግ ቤተ ክርስቲያናችን ከችግር ነፃ ለማድረግ ጊዜ እሩቅ አይሆንም ቤተ ክርስቲያን ነፃ ወጣች ማለት መላ ኢትዮጵያ ነፃ ወጣች ማለት እንደሆነ አምናለሁ፡፡

ከዚህም በአሻገር«ሑሩ ወመሐሩ ኵሎ አሕዛበ»በአለው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት በኢትዮጵያውያን ስደተኞች አማካይነት«ወብየ ካልአትኒ አባግዕ እለ ኢኮና እምዝንቱ ዐጸድ ወኪያሆንሂ ሀለወኒ አምጽኦን ዝየ» እንደለው ወንጌሉ በኬንያ የቱርካና በሔረ ሰብ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ እምነት በመቀበል ወደ እምነቱ እየጎረፉ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶላቸው እያገለገሉም እየተገለገሉም ናቸው እነሱንም በእምነታቸው እንዲጸኑ በምግባራቸው እንደበረቱ በምጣኔ ሀብት በማኅበራዊ ሕይወታቸው የሚደገፉበትንና የሚረዱበትን መንገድ ማመቻቸትና ከርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተላከው እርዳታ ለልጆቻቸው የሚማሩበት ት/ቤት እንዲጀመርበት በመሆኑ ያን ማስፈጸምና ማሳደግ እንዲሁም በአካባቢው ልማት ነክና ጤና ጣቢያ እንዲኖራቸው ማድረግ ቢቻል «ኦ ገብር ወምዕመን ዘበውሁድ ምዕመነ ኮንከ ዲበ ብዙህ እሰይመከ» የሚለው የምስጋና ዜና ሰሚዮች ያደርገናል ብየ አምናለሁ።

2. ታሪከዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን የሚለው አረፍተ ነገር እውንነቱን አጥቶ በነበር እየተመዘገበ የአለበት ሁኔታ ላይ ነው የአለነው።ለዚህ ሁሉ መነሻውና መድረሻው የቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች ከጥቂቶቹ በቀር ብዙዎቹ የገቡትን ቃል በአለማክበራቸው መመርያቸውን በአለመከተላቸው መንጋዎቻቸውን ማስማራት በአለመቻለቸው ሰማያዊውን ዘንግተው ምድራዊውንና ኃለፊውን ብቻ ሙጥኝ በማለታቸው በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአለሁለት ፓትርያርክ በአለ ሁለት ሲኖዶስ በመሆንዋ ሁሉም ተወጋግዘው ሁሉም በእስራት የአሉ ናቸው ምንም እንኳን ጥናታዊ መረጃም ባይኖረኝ መንግስት በአወጣው እስታስቲክ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ እምነት ተከታይ በመቶ ስምንት መቀነስ እንዱ ይህ ነው ብዬ እገምታለሁ።በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችንን ብሔራዊትነቷንና ታሪከዊትነቷን እንደነበረ እንዲጓዝ ለማድረግ ሁለቱ ፓትርያሪኮች ዛሬ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ተገናኝተው በመነጋገር እርቅ በማድረግ ይቅር መባባል ሕዝበ ክርስቲያኑን ለብሔራዊ እርቅና ይቅርታ ማዘጋጀት ካህናትና ምዕመናን እንደ ፈትልና ሰም እንደእጅና ጓንት በመሆን ግዴታቸውንና ኃለፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ሲችሉ ብቻ ነው ምዕመናን አስራታቸውንና በኩራታቸውን ሲያወጡ ካህናት ለመንፈሳዊ አገልገሎት ለስብተ ወንጌል ሲተጉ ብቻ እንደሆነ ነው ጥናቱ የሚያሳየው ይህ ከአልሆነ ግን የአማንያን ቁጠር የበለጠ እየሸቆለቆለ መሄዱን ብሔራዊት ተሪካዊት የሚለውም ተረት ተረት ሆኖ እንዳይቀር ሥጋታዊ ግምትም አለኝ ።

በዚህ በሁለቱ አባቶች እርቅ ዙርያ በሰሜን አሜሪካ የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ በዋሽንግተን ዲሲ ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአደረገው አጠቃላይ ጉባኤ አንድ የአስታራቂ ኮሚቴ ማቋቋሙና በዚያ ዙርያ ኮሚቴው ጥረት እያደረገ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን የኢትየጵያ ሕዝበ ክርስቲያንም በዚህ ላይ ትልቅ ሚና አለው ይህ ተግባራዊ እንደሆን በጸሎት ማገዙ እንዳም ሲል እርቅ በማይፈልገው ይቅርታ በማያደርገው ላይ ተጽእኖ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታው እንደሆነ ሊያውቅ ይገበዋል፡፡በዚህ ዘመን የአለን ካህናትና ምዕመናን ቤተ ክርስቲያናችን በዚህ ዓይነት ሁኔታ እያለች ዝም ብለን ብናሳልፍ በዚህ ዘመን ብቻ በመኖራችን ታሪክ እንደሚወቅሰን እግዚአብሔርም በሰጠን መክሊት ስለአልተጠቀምንበት« ኦአግብርት ሀካያን» ብሎ ይፈርድብናል ብየ እፈራለሁ፡፡

3. ከአዲስ አበባ እሰከ ጂማ ከጅማ ኤሉባቡር እሰከ ጋምቤላ ከአዲስ አበባ እስከ ወላይታ በአደረኩት የበጎ ፈቃድ የአገልገሎት ጉዞ በሪፖርቴ ላይ እንደ ተገለጸው በአክራሪውና በባእዳን በኩል የአለው እንቅስቃሴ አይሎ ከመታየቱም በላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶከስ ቤተ ክርስቲያን ላይና እምነቱን በሚከተሉት ላይ ተጽኢኖ እያደረገ ይታያል፡፡እነሱ ይህን የበላይነትን እዲያገኙ ያበቃቸው በኅብረተ ሰቡ መካከል በመግባት በቋንቋው በማስተማራቸው በምጣኔ ሀብትና በማኅበራዊው ሕይወቱ ስለሚንከባከቡትና ስለሚደርሱለት መሆኑንም ተረድቻለሁ፡፡

በዚህ ዙርያ የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ኪዳን ምሕረት ገዳምና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ቤተ ክርስቲያን ጽርሐ ጽዮን ዘተዋኅዶ የአንድነት ኑሮ ማኅበር በዚህ ወቅት ቤተ ክርስቲያኒቷን ለማዳን ግንባር ቀደም በመሆን የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የሚደነቅና የሚደገፍ ነው በደቡቡ ክፍል ያገለግሉ የነበሩ ከሰሜን የመጡ ካህናት ስለነበሩ ችግር በተከሰተ ጊዜ እየጣሉ በመሔዳችው በጂማ ሀገረ ስብከት 270 አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ በቂ አገልግሎት የሚሰጡት 79 ብቻ ናቸው 191 ደግሞ የተዘጉና የተሟላ አገልገሎት እንደማይሰጥባቸው የአወጡት ቅጽ ያመለክታል ይህንን ለሟሟላት የተወሰደው እርምጃ ከየብሔረ ሰቡ ህጻናትን በማሰባሰብ 45 ህፃናት በአበልቲ ኪዳን ምሕረት ገዳም በመማር ላይ ይገኛሉ እነዚህም የሚሰለጥኑት ለሶስት ዓመታት ያህል ነው እያንዳዱ ተማሪ በወር የሚያስፈልገው ከ20 እስከ 25 ዶላር ብቻ ነው

ቁጥራቸውን ከፍ ለማድረግ መኖርያ ቤታቸው እየተጠናቀቀ ይገኛል በግልም ሆነ በማኅበር እነዚህን መርዳት ክርስቲያናዊ ግዴታን መወጣት ነው፡፡ እንዲሁም ከኬንያ ከቱርካናው ብሔረ ሰብ ሦስት ህፃናትን አሰልጥኖ ወደዚያው መልሶ ለመላክ ብፁዕ አባታችን አቡነ እስጢፋኖስን ጠይቀን ለትምህርታቸውና ለመኖርያቸው በነጻ እናሥተምራቸዋለን ምግባቸው ከተቻለ ብለውናል ስለዚህ ሦስቱን የቱርካና ብሔረ ሰብ ዲያቆናት አንድ አንዱን አንዱን ለሁለት ለሶስት እችላላሁ የሚትሉ ሁሉ በጎ ፈቃዳችሁንና እርዳታችሁን ብታደርጉ ሃይማኖታዊ ግዴታችሁን ተወጥታችኋልና ደስ ይበላችሁ እንላለን ለአንዱ በወር 20 በዓመት 240 ወይም በወር 25 በዓመት 300 በሦስት ዓመት 900 ዶላር ወይም 720 መሆኑን በትህትና እንገልጻለን፡፡

ጽርሐ ጽዮን ዘተዋኅዶ የአንድነት ማኅበርም ገና ከጅምሩ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ከጠቅላላው ኢትዮጵያ ከአሉት ሀገረ ስብከቶች ከተለያዩ ብሔረ ስብ ቢያንስ አንድ ሠልጣኝ ሁለት ሦሰት የሀገር ውስጥ ቋንቋዎች መናገር የሚችለውን ከቤተ ክርስቲያን ልጆች መካከል በመምረጥ አሰባስቦ በየክረምቱ የሁለት ወራት ኮርስ በመስጠት በስብከተ ወንጌል በማሰልጠን አስመርቆ ወደ የመጡበት ብሔረ ሰብ ተመልሰው በየቋንቋው ብሔረ ሰባቸውን እያገለገሉ እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ፡፡

ማኅበሩ አሁንም ለዚሁ ጉዳይ ቅድምያ በመስጠት ከእጅ ወደ አፍ የአለው ኑሮው ሳያግደው እግዚአብሔርን በማመን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖችን ተስፋ በማድረግ  ዓመት አስከ ዓመት በየሦስት ወሩ እየሰለጠኑ የሚወጡበት ማሰልጠኛ መኖርያውንም ሆነ መማርያ ክፍሉንና ለአንድ ማሰልጠኛ የሚስፈረልገውን አሟልቶ የያዘ ህንጻ ጀምሯል ሥራው እየተሠራ አንደኛው ፎቅ አልቆ ሁለተኛው በጅምር ላይ ይገኛል የሚያንሰው ተገባዶ ለመጨረስ የቀረው የሚበልጠው በመሆኑ በውጪ የአለችው ቤተ ክርስቲያን ይህ ሃይማኖታዊ ድርጅት ለቤተ ክርስቲያናችን እንደ ደም ሥር ሆኖ ስለአገኘሁት ህንፃውን በማስፈጸምም ሆነ ኮርሱ በተከታታይ ሳያቋርጥ እንዲጓዝ በማድረጉ ዙርያ ከእኛ የጸሎት የኃሣብ የጉልበት የውቀትና የገንዘብ እርዳታ ያሰፈልጋቸዋል፡፡እዚህ የአሉ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ምሑራን የእረፍት ጊዜያቸውን በማመቻቸት እዚያ በመገኘት አገልግሎት ቢሰጡ ደግሞ የበለጠ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመታደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብየ አምናለሁ፡፡ ለዚህ ሁሉ የአምላካችን ፈቃድ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነትና ተራዳኢነት አይለየን ፡፡ አሜን ፡፡

# ምሥጋና

«በሉ አግብርት ፅሩዓን ንሕነ ወዘይደልወነ ለገቢር ገበርነ» በሚለው ወንጌሉ ቃል መሠረት አመስጋኝና ተመስጋኝ ባይኖርም የተደረገላቸው እነዚህን አስነስቶ እንዲህ በማደርጉ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ አድራጊዎችም የእነሱ የአልሆነውን ከእግዚአብሔር የአገኙትን መልሰው በመስጠታቸው ሳይወዱ በግድ ትተውት የሚሄዱትን በሕይወት እያሉ ዓይናቸው እያየ እንዲያደርጉ ስለፈቀደላቸው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ በመስጠቱም ሆነ በመቀበሉ ዙርያ የሌሉ ተስፋቸው ይህን ዓለም ብቻ አድረገው የሚኖሩት ደግሞ ይህንን ሲያዩና ሲሰሙ ለካስ ይህ አለ ብለው ወደ ህሊናቸው እንዲመለሱ እንኪን የአላቸው ንብረታቸው ቀርቶ ስውነታቸው የእነርሱ አለመሆኑን እንዲረዱና ወደ ንስሐ እንዲመለከቱ ስለሚያደርጋቸው ነው ጠቢቡ ሰሎሞን «ወድሶ ለሰብእ በዘኢኮነ ድልዎቱ» የአለውም ከዚህ ተነስቶ እንደሆነ ተርጓሚ አያሻውም፡፡ እኔም ከዚህ ተነስቼ ነው ለማመስገን የተገደድኩት፡፡

1. በመጀመርያ ይህንን ጉዞ አመቻችቶ ፈቃዱን ከፈቃዱ ጋር በማገናኘ ት ህሊናዬን በማነሳሰት በሄድኩባቸው በተጓዝኩባቸው ሁሉ ሳይለየኝ በሰላም ደርሺ እንደ መለስ የረዳኝን አምላኬን አመሰግንዋለሁ፡፡

2. የርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ከሁሉም በላይ ቅድምያ በመስጠት ሀገርን ሕዝብን ወገንን በመርዳት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ የእኔን መሄድ በማወሳት ፈቃድ የአስተዳደሩን ቦርድ ስጠይቅ ይህንኑ መነሻ በማድረግ ፈቃድ ከመስጠት ጋር አስፈላጊውን በማደረግ እንዲሁም ለካኩማ ስደተኞች ከምዕመናን ቀደም ሲል የተሰብስቦ ሳይላክ የቆየውን አራት ሺ ዶላር ስለፈቀደልኝና እዚያ ወሰጄ በመስጠቴ ስደተኞቹም ሆኑ የቱርካናው ብሔረ ሰብ ሳይቀር አስታዋሽ የአልነበራቸው አስታዋሽ በማግኘታቸው የተሰማቸውን ደስታ

እንደስተላልፍላቸው ስለጠየቁኝ በራሴም በእነሱም ስም ሆኜ የባለአደራውን ቦርድ አመሰግናለሁ፡፡

3. ለጉዞየ የሚሆነውን ሁሉ ከማመቻቸት በአሻገር በጉዞየ ሁሉ ሳትለይ ዋዕየ ፀሐዩ ሳይበግራት አቀበቱን መውጣት ቁልቁለቱን መውረድ ሳይሰለቻቻት አብራኝ የተገኝዘቸውን (ሥርጉተ ገብርኤልን) ራኄል መኩርያን ከልብ በማመስግን እግዚአብሔር ይባርክሽ የልብሽን መሻት ይስጥሽ እላለሁ፡፡

4. በገዳመ ተክለ ሃይማኖት የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ ቀደም ሲል በካኩማ ዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሲታነጻ ለህንፃው ድጋፍ ለቤተ ልሔሙ ማስርያና ኩታ ገጠም የሆነውን ቦታ መግዣ ስድስት ሺ ዶላር የገንዘብ እርዳታ ከማደረጉም በአሻገር አሁን ወደ እዚያ በምሄድበት ወቅት ለአንዳንድ አስፈለጊ ጉዳዮች እንዲሆናቸው ሁለት ሺ አምስት መቶ ዶላር በመላኩ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ገንዘቡ በመድረሱ አመስግነው ምስጋናቸውን ለኮሚቴው እንዳስተላልፍለቸው ስለጠየቁ የአደረገውን ሃይማኖታዊና ሰብአዊ እርዳታ በማድነቅ በእነሱ ስም ምሰጋናቸውን አቀርባለሁ፡፡

5. ብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ የጅማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ከአዲስ አበባ ጅማ ከጅማ ኤሉባቡር ጋምቤላ ከፋ ሚዛን ተፈሪ አቡነ ሐራ ድንግል በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ ስጓዝ መኪናቸውን ሹፌራቸውንና ነዳጁ ሳይቀር በማሟላት ስለፈቀዱልኝ ከልብ እያመሰገንሁ ለብፁዕነታቸው ሙሉ ጤና ሰጥቶ በአገልግሎታቸው ሁሉ እንዳይለያቸው እየተመኘሁ እንደዚህ ከአሉ የቤተ ክርስቲያን ችግር ቀድሞ የሚገባቸው ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሔ የሚሰጡ የአለንበት ዘመን የገባቸው አባት ጋር እንደገናኝ የፈቀደ አምላኬን አመሰግናለሁ፡፡
6. አዲስ አበባ ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተመለስኩበት ድረስ በቤታቸው በመቀበል አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ ለተቀበሉኝና ለአስተናገዱኝ ወገኖቼ ወ/ሮ ጽጌ ግርማና ባለቤታቸው አቶ አደላ ልዑል ሰገድን ከልብ አመሰግናለሁ ቤታችሁን ይባርክ ጤናችሁን አብዝቶ ይስጥልኝ፡፡

7. ባለቤቴ ወ/ሮ ነገደ ግርማና የመንፈስ ልጆቼ አባታችን ወደ ኢትዮጵያ ሲሄድ እጅ እጁን የሚመለከቱ እሱም ተጎሳቁለውና ተቸግረው የሚያያቸው አብያተ ክርስቲያናት ገዳማት ገዳማውያን ዝም ብሎ ዓይቶ ከነፈሩን መጦ እንዳይመለስ የሚችለውን እንዲረዳ ብላችሁ ከእኛ ችግር የእሱ ችግር ይበልጣል በማለት የለገሳችሁት ገንዘብ ከችግሩ ጽናት ከችግረኛው ብዛት የተነሳ ለሁሉም መድረስ ባይቻል በሄድኩበት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን የሚሆነውን ለቤተ ክርስቲያን ለችግርኛ የሚውለውንም ለዚያው የሚያስፈለገውን በማደረግ ሳልሰቀቅ ምን እሰጥ ብዬ ኃፍረት ሳየሰማኝ የሄድኩበትን አገልገሎት ፈጽሜ በሰላም እንድመለሰ ለአደረጋችሁ የመንፈስ ልጆቼ በሙሉ ከልብ አመሰግናችኂለሁ በሰጣችሁት ይተካላችሁ የምትሰጡት አያሳጣችሁ አምላከ ነዲያን በነፍስ በሥጋ ይጠብቃችሁ ጻህቀ ልቡናችሁን ሁሉ ይፈጽምላችሁ። አሜን

«ወስብሐት ለእግዚአብሔር»

<u>ግልባጭ</u>

ለብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ
ለብፁዕ አቡነ እስጢፋኖስ
ለአቡነ ሐራ ድንግል ማኅበር
ለጽርሐ ጽዮን ማኅበር
ለካኩማ ዳግማዊ ቁልቢ ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤ.ክ
ለደብረ ሊባኖስ ገዳም
በጫጋል የችግረኞች መንደር
በናይሮቢ ገ.ተ.ሃ. የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ቅርጫፍ
በአዲስ አበባ ገዳመ ተክለ ሃይማኖት መ.ቅ.ማ ቅርንጫፍ
ለመንፈስ ልጆቼ ለየአንዳዳቸው

ሊ/ማ/ዶ/ር አማረ ካሣዬ